የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራአራተኛ ዓመት ቁጥር ፶፯
አዲስ አበባ ነሐሴ ፲፱ ቀን ፪ሺ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

14th Year No 57.
ADDIS ABABA 25th August, 2008

ማውጫ
አዋጅ ቁጥር ፭፻፶፪/፪ሺ ዓ.ም

የባንክ ሥራ አዋጅ ... ገጽ ፬ሺ፪፻

CONTENTS
Proclamation No. 592/2008

Banking Business Proclamation Page 4200

አዋጅ ቁጥር ፭፻፶፪/፪ሺ

ስለባንክ ሥራ የወጣ አዋጅ

ባንኮች ከሀገር ውስጥም ሆነ ከውጭ ሀገር ገንዘብ በማሰባሰብ በተለያዩ የልማት ዘርፎች እንዲውል በማድረግ በሀገሪቱ የኢኮኖሚ ልማት ከፍተኛ ሚና የሚጫወቱ በመሆናቸው፣

ባንኮች በሀገሪቱ ኢኮኖሚ የክፍያና የክፍያ አፈጻጸም ሥርዓት ውስጥ ቁልፍ ሚና ያላቸው በመሆ ናቸው፣

የባንክ ሥራ በተገቢው ሥርዓት አለመመራት በፋይናንስ ሥርዓቱና በአጠቃላይ ኢኮኖሚው ላይ ጎጂ የሆነ ያለመረጋጋት ሁኔታን የማስከተል ባህሪያት ያሉት በመሆኑ፣

በፋይናንስ ሥርዓቱና በአጠቃላይ ኢኮኖሚው ላይ የሚደርሰው አለመረጋጋት በሕዝብና በመንግሥት ላይ የሚያስከትለውም ጉዳት በቀላሉ የሚገመት ባለመሆኑ፣

የባንክ ሥራ ፈቃድ አሰጣጥና ቁጥጥርን በሚመለከት ሁለአቀፍ ሕግ በማውጣት የባንክ ሥርዓቱ ለአደጋ ያልተጋለጠ፣ አስተማማኝና የተረጋጋ መሆኑን ማረጋገጥ አስፈላጊ በመሆኑ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግሥት አንቀጽ ፶፭/፩/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

PROCLAMATION NO. 592/2008.

A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR BANKING BUSINESS

WHEREAS, banks play an important role in economic development through mobilization of funds from within and outside the country and channeling such funds to various sectors of the economy;

WHEREAS, banks occupy a central place in the payment and settlement system of the country's economy;

WHEREAS, the business of banking has a number of attributes which, if not managed properly, has the potential to generate financial system and macroeconomic instability;

WHEREAS, the cost of financial system and macroeconomic instability to the general public and the Government is significant;

WHEREAS, it is essential to ensure safety, soundness and stability of the banking system by having a comprehensive law for the licensing and supervision of the banking business;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

ክፍል አንድ
ጠቅላላ

፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የባንክ ሥራ አዋጅ ቁጥር ፭፻፺፪/፪ሺ" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጓሜ የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፣ በዚህ አዋጅ ውስጥ፤

፩/ "ባንክ" ማለት የባንክ ሥራ እንዲሠራ በብሔራዊ ባንክ ፈቃድ የተሰጠው ኩባንያ ወይም የመንግሥት ባንክ ነው፣

፪/ "የባንክ ሥራ" ማለት የሚከተሉትን ሥራዎች ያጠቃልላል፣

ሀ/ ብሔራዊ ባንክ ተቀባይነት አለው ብሎ በፈቀደው የገንዘብ መሰብሰቢያ ዘዴ ከሕዝብ ተቀማጭ ገንዘብ የመቀበል፣

ለ/ የባንክ ሥራ በሚሠራው ሰው ሂሣብና ኃላፊነት በዚህ ንዑስ አንቀጽ ተራ ፊደል /ሀ/ የተመለከተውን ገንዘብ በሙሉ ወይም በከፊል በብሔራዊ ባንክ ተቀባይነት ባለው ሁኔታ በብድሮች ወይም በኢንቨስትመንቶች ላይ የማዋል፣

ሐ/ በገንዘብ መልክ ያልተቀረፀ ወርቅና ብር እንዲሁም የውጭ ምንዛሪ የመግዛትና የመሸጥ፣

መ/ በባንኮቹ በራሳቸውም ሆነ በደንበኞቻቸው ስም ለሌሎች የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር ሰዎች ገንዘብ የማስተላለፍ፣

ሠ/ በገንዘብ ማስከፈያ፣ በሐዋላና በተስፋ ሰነዶች እንዲሁም በሌሎች የዕዳ ማረጋገጫ ሰነዶች አማካኝነት በቅናሽ የማበደርና የማስተላለፍ፣

ረ/ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ከተራ ፊደል "ሀ" እስከ "ሠ" በተመለከቱት ተግባራት የተሰማራ ባንክ እንዲሠራቸው በብሔራዊ ባንክ የሚፈቀድለት በተለምዶ እንደባንክ ሥራ የሚታወቁ ሌሎች ተግባሮችን የማከናወን፣

PART ONE
GENERL

1. Short Title

This Proclamation may be cited as "Banking Business Proclamation No. 592/2008".

2. Definitions

In this Proclamation unless the context requires otherwise:

1/ "bank" means a company licensed by the National Bank to undertake banking business or a bank owned by the Government;

2/ "banking business" means any business that consists of the following activities:

a) receiving funds from the public through means that the National Bank has declared to be an authorized manner of receiving funds;

b) using the funds referred to under paragraph (a) of this sub-article, in whole or in part, for the account and at the risk of the person undertaking banking business, for loans or investments in a manner acceptable by the National Bank;

c) the buying and selling of gold and silver bullion and foreign exchange;

d) the transfer of funds to other local and foreign persons on behalf of the banks themselves or their customers;

e) the discounting and negotiation of promissory notes, drafts, bills of exchange and other evidence of debt;

f) any other activity recognized as customary banking business, which a bank engaged in the activities described from paragraph (a) to (e) of this sub-article may be authorized to undertake by the National Bank;

፫/ "የካፒታል ወጪ" ማለት በመቋቋም ላይ ባለ ባንክ የሚከፈል የቅድሚያ ወጪ፣ የአክሲዮን ሽያጭ ኮሚሽን፣ የድለላ አገልግሎት ክፍያና በቋሚ ንብረት መልክ የማይታይ ሌላ ወጪ ነው፣

፬/ "ዋና የሥራ አስፈጻሚ" ማለት በማናቸውም የማዕረግ ስም የሚጠራ ቢሆንም የአንድን ባንክ የዕለት ተዕለት ሥራዎች በዋና ኃላፊነት የመምራት ሥልጣን የተሰጠው ሰው ነው፣

፭/ "ኩባንያ" ማለት በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ የተሰጠውን ትርጓሜ የያዘ ሆኖ አክሲዮኖቹ በሙሉ በኢትዮጵያውያንና በሙሉ በኢትዮጵያውያን ባለቤትነት በተቋቋሙ ድርጅቶች የተያዘ በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት የተመዘገበና ዋና መሥሪያ ቤቱ በኢትዮጵያ የሆነ አክሲዮን ማኅበር ነው፣

፮/ "ዳይሬክተር" ማለት በማናቸውም የማዕረግ ስም የሚጠራ ቢሆንም የባንክ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ነው፣

፯/ "ሠራተኛ" ማለት የባንክ የዕለት ተዕለት ሥራዎችን እንዲያካሂድ የተሾመ ወይም የተቀጠረ ዋና ሥራ አስፈጻሚ፣ ከፍተኛ ሥራ አስፈጻሚ ወይም ማንኛውም ሌላ ሰው ነው፣

፰/ "የአደራ ተግባር" ማለት አብዛኛውን ጊዜ የአገልግሎት ክፍያ በማስከፈል በባንክ የሚከናወን ንብረትን ተቀብሎ በአደራ የማስቀመጥ ወይም በሌሎች ሰዎች ስም ገንዘብ የማስተዳደር ተግባር ነው፣

፱/ "የፋይናንስ ድርጅት" ማለት መድን ሰጪ ኩባንያ፣ ባንክ፣ አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም፣ የፖስታ ቁጠባ ድርጅት፣ የሐዋላ ድርጅት ወይም በብሔራዊ ባንክ የሚወሰን ሌላ ተመሳሳይ ድርጅት ነው፣

፲/ "የሂሣብ ዓመት" ማለት እንደ አውሮፓውያን የዘመን አቆጣጠር ከጁላይ ፩ ቀን ጀምሮ በቀጣዩ ዓመት ጁን ፴ ቀን የሚያበቃ የባንክ የሂሣብ ዓመት ነው፣

፲፩/ "ተደማጭነት ያለው ባለአክሲዮን" ማለት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከማናቸውም ባንክ ጠቅላላ የተፈረመ ካፒታል ሁለት በመቶ ወይም ከዚያ በላይ የአክሲዮን ድርሻ ያለው ሰው ነው፣

3/ "capitalized expenditure" means preliminary expenses, share selling commission and brokerage fees paid by a bank under formation, and any other item of expenditure not represented by tangible assets;

4/ "chief executive officer" means a person, by whatever title that person may be referred to, who is primarily responsible for the day-to-day management of the affairs of a bank;

5/ "company"' means a share company as defined under the Commercial Code of Ethiopia, in which the capital is wholly owned by Ethiopian nationals and organizations wholly owned by Ethiopian nationals and registered under the laws of, and having its head office in, Ethiopia;

6/ "director" means any member of the board of directors of a bank, by whatever title he may be referred to;

7/ "employee" means a chief executive officer, a senior executive officer or any other person who is appointed or hired by a bank to carry out its day-to-day operational activities;

8/ "fiduciary function" means the trustee function of a bank whereby the bank provides safe keeping services or administers funds on behalf of others, usually for a fee;

9/ "financial institution" means insurance company, bank, micro finance institution, postal savings, money transfer institution or such other similar institution as determined by the National Bank;

10/ "financial year" means the financial year of a bank running from July 1st to June 30th of the following year;

11/ "influential shareholder" means a person who holds directly or indirectly two percent or more of the total subscribed capital of a bank;

፲፪/ "ዕዳ መክፈል የማይቻልበት ወሰን" ማለት ብሔራዊ ብንክ በሚወስነው መሠረት የማናቸውም ባንክ ጠቅላላ ዕዳ ከጠቅላላ ሀብቱ የበለጠ የሚሆንበት ጊዜ ነው፣

12/ "insolvent" means the financial condition of a bank when the liabilities of such bank exceed its assets as determined by the National Bank;

፲፫/ "ብድር" ወይም "ቅድሚያ ክፍያ" ማለት በተወሰነ ቀን ወይም ቀኖች ወይም በተጠየቀ ጊዜ በተለምዶ ከወለድ ጋር ተመልሶ እንዲከፈል ቅድመ ሁኔታዎችን በማስቀመጥ ወይም ግዴታ በማስገባት በቀጥታ፣ ወይም እንደአል ታቀደ አቨርድራፍት፣ ከሌላ አበዳሪ ጋር በት ብብር በሚሰጥ ብደር እንደመሳተፍና ከሌላ አበዳሪ ብድር እንደመግዛት በመሳሰሉት በተዘ ዋዋሪ ለማንኛውም ሰው ገንዘብ ከመስጠት ወይም ገንዘብ ለመስጠት ቃል ከመግባት የሚ መነጭ ማናቸውም የአንድ ባንክ የፋይናንስ ሀብት ሲሆን ማናቸውም ባንክ ለማንኛውም ሰው በቀጥታ ወይም በስሙ ብድር ለመስጠት፣ ባንኩ አከራይ በሆነበት የሊዝ ፋይናንስ ስምም ነት ማስረጃነት የይገባኛል መብትን ለማስተና ገድና በተበዳሪው ስም የአቨርድራፍት አገልግ ሎት ለመስጠት በውል ላይ ተመሥርቶ የተገ ባን ግዴታ ያጠቃልላል፣

13/ "loan" or "advance" means any financial assets of a bank arising from a commitment to advance funds by a bank to a person that is conditioned on the obligation of the person to repay the funds, either on a specified date or dates or on demand, usually with interest, or from indirect advances such as unplanned overdrafts, participation in loan syndication and the purchase of loans from another lender; and includes a contractual obligation of a bank to advance funds to or on behalf of a person's claim evidenced by a lease financing transaction in which the bank is the lessor, and an overdraft facility to be funded by a bank on behalf of a person;

፲፬/ "ሰው" ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፣

14/ "person" means any natural or juridical person;

፲፭/ "የችሎታ መመዘኛ" ማለት ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣው መመሪያ የሚወሰን ተፈላጊ የትምህርት ደረጃ፣ የሥራ ልምድ፣ የብቃትና የሥነ-ምግባር መመዘኛ ነው፣

15/ "qualification of competency" means required education, experience, fitness and propriety determined by the directive to be issued by the National Bank;

፲፮/ "ሞግዚት" ማለት ብሔራዊ ባንክ ወይም ችግር ያለበትን ባንክ በመረከብ አሠራሩን እንደገና በማዋቀር ጤናማ ለማድረግ ወይም ሕልውናው እንዲያከትም ለማድ ረግ በብሔራዊ ባንክ የተሾመ ሰው ነው፣

16/ "receiver" means the National Bank or a person appointed by the National Bank to take control of a bank having problem for purposes of restructuring the bank's operations in order to make it sound or to terminate its existence;

፲፯/ "በዋስትና የተጠበቀ የይገባኛል ጥያቄ" ማለት በንብረት መያዣነት ወይም በውል መሠረት በሌሎች ንብረቶች ላይ ተፈጻሚ በሚሆን ዋስትና የተደገፈ የማናቸውም ባንክ የይገባኛል ጥያቄ ነው፣

17/ "secured claim" means any claim of a bank guaranteed by property or secured by assignment of rights to other assets on the basis of a contract to that effect;

፲፰/ "ከፍተኛ የሥራ አስፈጻሚ" ማለት የዋና ሥራ አስፈጻሚ ምክትል የሆነ ወይም ተጠሪነቱ በቀጥታ ለዳይሬክተሮች ቦርድ የሆነ ማንኛውም የባንክ የሥራ ኃላፊ ነው፣

18/ "senior executive officer" means any officer of a bank who is deputy to the chief executive officer or is directly reporting to the board of directors;

፲፱/ "ብሔራዊ ባንክ" ማለት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ነው።

19/ "National Bank" means the National Bank of Ethiopia.

ክፍል ሁለት
ስለባንክ ሥራ ፈቃድ

፫. ፈቃድ የማውጣት አስፈላጊነት

፩/ በብሔራዊ ባንክ የተሰጠ የባንክ ሥራ ፈቃድ ካልተያዘ በስተቀር በኢትዮጵያ ውስጥ የባንክ ሥራ ማካሄድ ክልክል ነው።

፪/ ማንኛውም ሰው ከብሔራዊ ባንክ ፈቃድ ሳያገኝ "ባንክ" የሚለውን ወይም ተዛማጅ የሆነ ስያሜ የማናቸውም የፋይናንስ ተቋም ስም አካል አድርጎ መጠቀም አይችልም።

፫/ ከብሔራዊ ባንክ በቅድሚያ የጽሑፍ ፈቃድ ካላገኘ በቀር ማንኛውም ባንክ፣

ሀ/ ብሔራዊ ባንክ ከፈቀደው ቦታ ውጭ የባንክ ሥራ ማካሄድ ወይም ነባር የሥራ ቦታን መዝጋት፣

ለ/ አዲስ የባንክ አገልግሎት መጀመር፣

ሐ/ ከሌላ ባንክ ጋር መቀላቀል ወይም የሌላ ባንክን ሥራ በባለቤትነት መያዝ፣

መ/ በመቀላቀልም ሆነ በሌላ መንገድ የባንኩን መሸጥ ወይም የባለሀብትነት መተላለፍ የሚያስከትሉ ማናቸውንም ዓይነት ስምምነቶች ወይም ውሎች ማድረግ ወይም የተፈቀደለትን የባንክ ንግድ ሥራ ዓይነት መቀየር፣

ሠ/ በመደበኛ የሥራ ተግባሩ አፈጻጸም ሳቢያ ካልሆነ በቀር የንብረት ባለቤት ነቱን በሙሉም ሆነ በከፊል በኢትዮጵያ ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገር ማስተላለፍ ወይም በሌላ መንገድ ማዛወር፣

ረ/ ባንኩ ራሱ ያወጣውን አክሲዮን መልሶ መግዛት ወይም በመደበኛ ተግባሩ በተከሰተ ኪሣራ ምክንያት ካልሆነ በቀር ካፒታሉን መቀነስ፣

ሰ/ የመመስረቻ ጽሑፉን ወይም የመተዳደሪያ ደንቡን ማሻሻል፣ ወይም

ሸ/ የባንክ ሥራ እንዲያካሂድ ፈቃድ ያገኘበትን ስም መቀየር፣ አይችልም።

PRAT TWO
LICENSING BANKING BUSINESS

3. Requirement of Obtaining License

1/ It is prohibited to transact banking business in Ethiopia without obtaining a banking business license from the National Bank.

2/ No person shall use the word 'bank' or its derivatives as part of the name of any financial institution unless it has obtained a license from the National Bank.

3/ Without the prior written approval of the National Bank, no bank shall:

a) transact a banking business at any place other than that authorized by the National Bank, or close an existing place of business;

b) introduce new banking services;

c) merge with or take over the banking business of another bank;

d) enter into any arrangement or agreement for the sale or disposal, by amalgamation or otherwise, of its business, or effect major changes in its line of business;

e) transfer or otherwise dispose of the whole or any part of its property, whether in or out of Ethiopia, other than in the normal course of its business;

f) redeem its own shares or effect a reduction of its capital other than through reduction due to operating losses;

g) amend its memorandum and articles of association; or

h) alter the name under which it is licensed to do banking business.

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ የተደነገገውን በመተላለፍ ማንኛውም ሰው ተቀማጭ ገንዘብ ለመቀበል በማስታወቂያ ወይም በማግባቢያ ዘዴ መጠቀሙን ወይም የባንክ ሥራ እያካሄደ መሆኑን ብሔራዊ ባንክ ለማመን ምክንያት ሲኖረው ይህንኑ ሁኔታ ለማጣራት ባንኩ በዚሁ ሰው ይዞታ ሥር የሚገኙትን የንግድ መዝገቦች፣ ቃለ-ጉባኤዎች፣ ሂሣቦች፣ ጥሬ ገንዘብ፣ የዋስትና ሰነዶች፣ ማስታወሻዎች፣ የገንዘብ ማዘዣዎችና ሌሎች ሰነዶች እንዲያቀርቡለት ማድረግና መመርመር ወይም ማስመርመር ይችላል።

4/ Where the National Bank has a reason to believe that a person, in contravention of sub-article (1) of this Article, is advertising for or soliciting deposits of money or transacting banking business, it may, in order to ascertain the situation, require that all books, minutes, accounts, cash, securities, records, vouchers and other documents which are in the possession or custody of such person be submitted to it and inspect the same or cause the same to be inspected;

፭/ ማንኛውም ሰው ያለፈቃድ የባንክ ሥራ በማካሄድ በዚህ ድርጊት አማካኝነት የተቀበለው ገንዘብና ሌላ ንብረት በእጁ የሚገኝ ከሆነ ብሔራዊ ባንክ ይኸው ገንዘብና ንብረት ለአስቀማጮቹ ወይም ለባለንብረቶቹ በአፋጣኝና በተቀላጠፈ መንገድ እንዲመለስ አስፈላጊው ትዕዛዝ እንዲሰጥበት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሊያመለክት ይችላል።

5/ Where any person undertakes banking business without license and holds moneys or other property obtained through such act, the National Bank may apply to the Federal High Court for ordering the immediate and efficient return of such moneys or property to the depositors or owners thereof.

፬. የፈቃድ ቅድመ ሁኔታዎች

4. Preconditions of Licensing

፩/ የባንክ ሥራ ፈቃድ ለማግኘት የሚከተሉት ሁኔታዎች መሟላት አለባቸው፣

1/ The following conditions shall be fulfilled to obtain a banking business license:

ሀ/ በሚገባ የተሞላ የፈቃድ መጠየቂያ ቅጽና ብሔራዊ ባንክ የሚጠይቃቸው ሌሎች አባሪ ሰነዶች መቅረብ አለባቸው፣

a) a duly completed application in the prescribed format and other accompanying documents as specified by the National Bank shall be submitted;

ለ/ ማመልከቻ በሚቀርብበት ጊዜ በብሔራዊ ባንክ የተወሰነው የሰነድ መመርመሪያ ክፍያ መከፈል አለበት፣

b) an investigation fee, as determined by the National Bank, shall be paid at the time of submitting the application;

ሐ/ ማመልከቻው ለብሔራዊ ባንክ እንደቀረበ ባንኩ በሚወስነው ቅጽ መሠረት መሥራቾቹ በባንክ ሥራ ለመሰማራት መፈለጋቸውን ለአራት ተከታታይ ሳምንታት ቢያንስ በሳምንት አንድ ጊዜ በስፋት በሚሠራጩ ጋዜጦች ላይ አሳትመው ማውጣት አለባቸው፣

c) upon filing the application with the National Bank, the founders shall, at least once a week for a period of four consecutive weeks, publish, in a form prescribed by the National Bank, a notice of intention to engage in banking business in widely circulating newspapers;

መ/ ባንኩ በኩባንያ መልክ መቋቋምና የመመሥረቻ ጽሑፉና የመተዳደሪያ ደንቡ በሚመለከተው የመንግሥት አካል ከመመዝገቡ በፊት በብሔራዊ ባንክ መጽደቅ አለበት፣

d) the bank shall be formed as a company and its memorandum and articles of association shall be approved by the National Bank before registration with the appropriate government organ;

ሠ/ ያወጣቸው አክሲዮኖች በሙሉ የተፈረሙ ሆነው ከእነዚሁም ውስጥ ቢያንስ ሩቡ በጥሬ ገንዘብ የተከፈለ መሆን አለበት፣

e) all its issued shares shall be subscribed and, at a minimum, one-fourth of the subscribed shares shall be fully paid in cash;

ረ/ በብሔራዊ ባንክ የተወሰነው ዝቅ ተኛ የተከፈለ ካፒታል በጥሬ ገን ዘብ መክፈልና በምሥረታ ላይ ባለው ባንክ ስም በዝግ የባንክ ሂሳብ ውስጥ መቀመጥ አለበት፣

ሰ/ የባንኩ ዳይሬክተሮች፣ ዋናው ሥራ አስፈጻሚና ከፍተኛ ሥራ አስፈጻ ሚዎች ብሔራዊ ባንክ ያወጣውን የችሎታ መመዘኛ የሚያሟሉ መሆን አለባቸው፣

ሸ/ ተደማጭነት ያላቸው ባለአክሲዮ ኖች ብሔራዊ ባንክ ያወጣውን የተገቢነትና ሥነ-ምግባር መመዘኛ የሚያሟሉ መሆን አለባቸው፣

ቀ/ የባንኩ ሕንፃና ግቢ፣ የጥበቃ ሥርዓትና የገንዘብ ማስቀመጫ ቮልት ብሔራዊ ባንክ ያወጣቸውን መስፈርቶች አሟልተው መገኘት አለባቸው።

፪/ ሊቋቋም በታሰበው ባንክ ውስጥ የማንኛውንም መሥራች ባለአክሲዮን መሆን የሚቃወም ማንኛውም ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩/ሐ/ በተመለከተው መሠረት የመጨረሻው ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በሰላሳ ቀናት ውስጥ ተቃውሞውን ከማስረጃ ጋር በጽሑፍ ለብሔራዊ ባንክ ማቅረብ ይች ላል። ብሔራዊ ባንክ ተቃውሞውን ለመ መርመር የሚያስችል እርምጃ ይወስዳል። የምርመራው ውጤት በጋዜጣ ታትሞ እንዲ ወጣ ተደርጎ ፈቃዱን ለመስጠት ወይም ለመከልከል ታሳቢ ይደረጋል።

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ የተዘረዘሩት እንደተጠበቁ ሆነው፣ የባንክ ሥራ ፈቃድ ተጨማሪ ግዴታዎችን ለመደንገግ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

፭. ፈቃድ ስለመስጠት

፩/ ብሔራዊ ባንክ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፬ መሠረት መቅረብ ያለባቸው መረጃዎች ተሟልተው ከቀረቡበት ቀን ጀምሮ ባሉ ፺ ቀናት ውስጥ በባንክ ሥራ ፈቃድ ማመልከቻው ላይ ውሳኔ ይሰጣል።

፪/ ፈቃዱ የሚሰጠው በብሔራዊ ባንክ የተወሰነው የፈቃድ ክፍያ ሲከፈል ይሆናል።

f) the minimum paid-up capital prescribed by the National Bank shall be paid in cash and deposited in a blocked account in a bank in the name of the prospective bank;

g) the directors, the chief executive officer and senior executive officers of the bank shall meet the qualification criteria prescribed by the National Bank;

h) influential shareholders of the bank shall meet the fitness and propriety criteria prescribed by the National Bank; and

i) the premises, security arrangements and cash vault of the bank shall meet the standards prescribed by the National Bank.

2/ Any person who objects the involvement of any of the founders as a shareholder in the proposed bank may submit, no later than thirty days starting from the date of the last publication under sub-article 1(c) of this Article, his objection in writing, with supporting evidence, to the National Bank. The National Bank shall initiate an inquiry into the objection. The results of such an inquiry shall be published and be considered in deciding whether or not to issue the license.

3/ Without prejudice to the requirements specified under sub-article (1) of this Article, the National Bank may issue directive to prescribe additional conditions of licensing.

5. Issuance of License

1/ The National Bank shall decide on a banking business license application within 90 days from the last date of receipt of all information to be submitted in accordance with Article 4 of this Proclamation.

2/ The license shall be issued upon payment of the licensing fee determined by the National Bank.

፫/ በዚህ አዋጅ መሠረት በብሔራዊ ባንክ የተሰጠ ፈቃድ የባንክ ሥራን ለማካሄድ የሚያስችል የመጨረሻው ፈቃድ ይሆናል።

፬/ ብሔራዊ ባንክ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፬ ንዑስ አንቀጽ /፫/ መሠረት የፈቃድ ሁኔታዎችን ሲያሻሽል ማሻሻያው በሥራ ላይ እንዲውል ከታሰበበት ጊዜ ሠላሳ ቀን ቀደም ብሎ የሚመለከታቸው ባንኮች እንዲያውቁት ያደርጋል።

፮. የባንክ ሥራ ስለመጀመር

ፈቃድ የተሰጠው ባንክ፣

፩/ ሥራ ከመጀመሩ በፊት በብሔራዊ ባንክ በሚወጣው መመሪያ መሠረት ብቃት ያለው የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት፣ የመረጃ ፍሰት ሥርዓት፣ የሪስክ ማኔጅመንት ፖሊሲና ደንቦች፣ እንዲሁም የሰው ኃይል አደረጃጀትና የመሳሰሉትን የባንክ ሥራ ለማከናወን አስፈላጊ የሆኑ ግዴታዎችን ማሟላት፣ እና

፪/ ፈቃዱ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ባሉት ፲፪ ወራት ውስጥ ሥራ መጀመር፣ አለበት።

፯. የፈቃድ እድሳት

ብሔራዊ ባንክ የባንክ ሥራ ፈቃድ የሚታደስበትን ሁኔታ በመመሪያ ሊወስን ይችላል።

፰. ፈቃድ የተሰጣቸውን ባንኮች ስለማስታወቅ

ብሔራዊ ባንክ በዓመታዊ ሪፖርቱ ውስጥ ፈቃድ የተሰጣቸውን ባንኮች ዝርዝር አትሞ ያወጣል። እንዲሁም በዚሁ ዝርዝር ላይ የተጨመሩትን ወይም ከዝርዝሩ የተሰረዙትን ባንኮች ሰፊ ስርጭት ባላቸው ጋዜጦች ላይ ወዲያውኑ አሳትሞ ያወጣል።

፱. ክልከላ

የውጭ ሀገር ዜጎች ወይም በከፊልም ሆነ በሙሉ በውጭ ሀገር ዜጎች ባለቤትነት ሥር ያሉ ድርጅቶች ወይም የውጭ ባንኮች በኢትዮጵያ ውስጥ ባንኮች ወይም የባንክ ቅርንጫፎች ሊያቋቁሙ አይችሉም፤ በኢትዮጵያ ውስጥ በተቋቋሙ ባንኮች አክሲዮን መያዝም አይችሉም።

3/ A license granted by the National Bank pursuant to this Proclamation shall constitute final authorization to carry on a banking business.

4/ Where the National Bank amends the conditions of licensing in accordance with sub-article (3) of Article 4 of this Proclamation, it shall notify the amendments to the concerned banks thirty days before the date on which the amendment becomes effective.

6. Commencement of Operation

A bank to which a license is granted shall:

1/ fulfill, before commencing operation, sound information management and internal control systems, risk management policies and procedures, and human resource organization and such other essential obligations to carryout banking business as determined by the directive to be issued by the National Bank; and

2/ commence its operation within 12 months from the date of the issuance of the license.

7. Renewal of License

The National Bank may issue directive on conditions of renewal of banking business license.

8. Publication of Licensed Banks

The National Bank shall, in its annual report, publish the list of licensed banks. It shall also publish, in newspapers of wide circulation, any additions to or cancellations from the said list.

9. Prohibitions

Foreign nationals or organizations fully or partially owned by foreign nationals may not be allowed to open banks or branch offices or subsidiaries of foreign banks in Ethiopia or acquire the shares of Ethiopian banks.

ክፍል ሦስት
ስለአክሲዮኖችና የባለአክሲዮኖች ጉባዔ

፲. ስለአክሲዮኖችና የአክሲዮን መዝገብ

፩/ የባንክ አክሲዮኖች እኩል ዋጋ ያላቸው፣ አንድ ዓይነት የሆኑና የተመዘገቡ ተራ አክሲዮኖች ይሆናሉ።

፪/ ማናቸውም ባንክ ብሔራዊ ባንክ በሚወ ስነው መሠረት የባለአክሲዮኖችን ስም ዝርዝርና ድምጽ የመስጠት መብታቸውን የሚያሳይ የአክሲዮን መዝገብ ይይዛል።

፫/ ማንኛውንም ሰው ተደማጭነት ያለው ባለአክሲዮን ሊያደርግ የሚችል የአክሲዮን ዝውውር በአክሲዮን መዝገብ ከመመዝገቡ በፊት በብሔራዊ ባንክ መጽደቅ አለበት።

፬/ በአክሲዮን መዝገብ ላይ ያልተመዘገበ ማናቸውም የአክሲዮን ዝውውር ዋጋ አይኖረውም።

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፪/ የተመለ ከተው የአክሲዮን መዝገብ በባንኩ መደበኛ የሥራ ሰዓት ሕዝብ ያለክፍያ ማየት በሚችልበት ሁኔታ በባንኩ ዋና መሥሪያ ቤት ይቀመጣል።

፲፩. አክሲዮኖች የመያዝ ገደብ

፩/ ከኢትዮጵያ ፌዴራል መንግሥት በስተ ቀር፣ማንኛውም ሰው ብቻውንም ሆነ ከባለቤቱ ወይም እድሜያቸው ከ፲፰ ዓመት በታች ከሆኑ በአንደኛ ደረጃ ከሚዛመዳቸው ሰዎች ጋር በመሆን የማናቸውም ባንክ የተፈረመ ካፒታል ከአምስት በመቶ በላይ አክሲዮን ሊኖረው አይችልም።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ የተደነገገው ቢኖርም ከአነስተኛ የፋይናንስ ተቋም ወደ ባንክ ባደገ ኩባንያ ውስጥ ማናቸውም የክልል መንግሥት ሊኖረው የሚችለው የአክሲዮን መጠን ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

፫/ በማንኛውም ባንክ ውስጥ አክሲዮን ያላ ቸው ሰዎች በከፊል ወይም በሙሉ በባለ ቤትነት የያዙት ኩባንያ በባንኩ ውስጥ ሊኖረው የሚችለውን የአክሲዮን መጠን ብሔራዊ ባንክ ይወስናል።

፬/ በአንድ ባንክ ውስጥ ተደማጭነት ያለው ባለአክሲዮን በሌሎች ባንኮች አክሲዮን መያዝ አይችልም።

PART THREE
SHARES AND SHAREHOLDERS' MEETINGS

10. Shares and Register of Shares

1/ Bank shares shall be of one class and shall be registered as ordinary shares of the same par value.

2/ Every bank shall keep a register of share as determined by the National Bank and which shall show the names and voting rights of shareholders.

3/ Any transfer of share that makes any person influential shareholder shall be approved by the National Bank before such transfer is recorded in the register of sharer.

4/ Any transfer of shares that is not recorded in the register of share shall be null and void.

5/ The register maintained under sub-article (2) of this Article shall be open to the public, without charge, at the bank's head office during its normal working hours.

11. Limitations on the Acquisition of Shares

1/ No person, other than the Federal Government of Ethiopia, may hold more than five percent of a bank's total shares either on his own or jointly with his spouse or with a person who is below the age of 18 related to him by consanguinity to the first degree.

2/ Notwithstanding the provisions of sub-article (1) of this Article, the amount of shares that may be held by regional governments in a bank transformed from a micro-finance institution shall be determined by the directive to be issued by the National Bank.

3/ The amount of shares that may be held in a bank by a company, which is partially or fully owned by persons who have share in the bank, shall be determined by the National Bank.

4/ An influential shareholder of any bank may not acquire shares in other banks.

፫/ ማንኛውም ሰው ከባንክ በተገኘ ብድር የባንክ አክሲዮን ሊገዛ አይችልም።

፬/ ይህ አዋጅ በፀናበት ቀን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ ወይም /፬/ የተመለከቱትን አስፈላጊ ሁኔታዎች ያላሟላ ማንኛውም ሰው እነዚህን ሁኔታዎች ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣው መመሪያ በሚወሰነው ጊዜ ውስጥ ማሟላት አለበት።

፲፪. የባለአክሲዮኖች ጉባኤ

፩/ ብሔራዊ ባንክ፣

ሀ/ በማንኛቸውም የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ በታዛቢነት የሚሳተፍ ሰው ሊመድብ፣ እና

ለ/ የገንዘብ አስቀማጮችን ወይም የባለአክሲዮኖችን ጥቅም ለማስከበር ወይም የባንክ ክፍለ ኢኮኖሚውን መረጋጋትና ጤናማነት ለማረጋገጥ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ በመዋዕለ ባንኩን በሚመለከቱ ማናቸውም ጉዳዮች ላይ አወያይቶ ውሳኔ ማሰጠት፣ ይችላል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩/ለ/ በተመለከተው መሠረት ብሔራዊ ባንክ የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ የጠራ እንደሆነ፣

ሀ/ የስብሰባውን አጀንዳ ያዘጋጃል፣

ለ/ የብሔራዊ ባንክ ሠራተኛ ወይም በባንኩ የተሰየመ ሌላ ሰው ስብሰባውን ይመራል፣

ሐ/ የባለአክሲዮኖችን ጠቅላላ ጉባኤ ምልዐተ ጉባኤ እና በጉባኤው የሚተላለፉ ውሳኔዎችን በሚመለከት በንግድ ሕጉ ስለአክሲዮን ማኅበራት የተደነገጉት አግባብነት ያላቸው ድንጋጌዎች ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል፣

መ/ ከጉባኤው መካሄድ ጋር የተያያዙ ወጪዎች ጉዳዩ በሚመለከተው ባንክ ይሸፈናሉ።

፲፫. ደምጽ የመስጠት ገደብ

፩/ ብሔራዊ ባንክ በማናቸውም የባለአክሲዮኖች ስብሰባ፣

ሀ/ ማንኛውም ሰው ለሌላ ባለአክሲዮን እንደራሴ ሆኖ የሚሰጠውን የድምጽ መጠን፣ እና

5/ No person may buy shares of a bank using bank loans or advances.

6/ Any person who does not fulfill the necessary requirements set under sub-articles (1) or (4) of this Article on the effective date of this Proclamation shall comply with such requirements within a period of time to be determined by the directive to be issued by the National Bank.

12. Shareholders' Meetings

1/ The National Bank may:

a) assign observers to attend any general shareholders' meeting of a bank;

b) where it finds necessary in the interest of depositors or shareholders or the stability and soundness of the banking sector, call a general shareholders' meeting of a bank to discuss and resolve any issues related to the bank.

2/ Where the National Bank calls a general shareholders' meeting as stipulated under Sub- Article 1(b) of this article:

a) it shall prepare the agenda for the meeting;

b) its officer or any other person assigned by it shall preside over the meeting;

c) pertinent provisions of the Commercial Code with respect to quorum and resolutions of shareholders' meeting of a share company shall apply;

d) expenses incurred in relation to the meeting shall be borne by the concerned bank.

13. Limitations on Voting Rights

1/ The National Bank may limit:

a) the number of votes by proxy in any meeting of shareholders'; and

ለ/ ከባንኩ የተበደረ ማንኛውም ባለአክሲዮን የሚኖረውን ድምጽ፣
ሊገደብ ይችላል።

፪/ ብሔራዊ ባንክ ማንኛውም ተደማጭነት ያለው ባለአክሲዮን ባንኩ በመመሪያ የሚወስናቸውን የሥነ-ምግባርና ተገቢነት መስፈርቶች ማሟላት ያልቻለ እንደሆነ ድምጽ የመስጠት መብቱን ሊገድብበት ይችላል።

ክፍል አራት
ስለባንክ ዳይሬክተሮችና ሠራተኞች

፲፬. ስለዳይሬክተሮችና ሥራ አስፈጻሚዎች ሹመት

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፫/፩/ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ማንኛውም ዳይሬክተር በብሔራዊ ባንክ እምነት ታማኝ፣ ሀቀኛ፣ ጠንቃቃና መልካም ዝና ያለው መሆን አለበት።

፪/ የባንክ ሥራ ፈቀድ በሚሰጥበት ጊዜም ሆነ በሌላ ማናቸውም ጊዜ የሚደረግ የማናቸውም ባንክ ዳይሬክተር፣ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ወይም ከፍተኛ ሥራ አስፈጻሚ ሹመት በብሔራዊ ባንክ በጽሑፍ ካልጸደቀ በስተቀር ተቀባይነት አይኖረውም።

፫/ ብሔራዊ ባንክ አዲስ የተመረጡ የባንክ ዳይሬክተሮችን ሹመት በጽሑፍ እስኪያ ጸድቅ ድረስ የነባር ዳይሬክተሮች የሥራ ዘመን ሳይቋረጥ መቀጠል አለበት።

፬/ ብሔራዊ ባንክ፣

ሀ/ ዳይሬክተሮች ማሟላት ስለሚገባቸው የችሎታ መመዘኛዎች፣

ለ/ የአንድ ባንክ የቦርድ አባሎች ሆነው የሚሠሩትን ዳይሬክተሮች ዝቅተኛ ቁጥር፣

ሐ/ የባንክ ዳይሬክተሮች ቦርድን ተግባራት፣ ኃላፊነት፣ ግዴታዎችንና መልካም የኩባንያ ሥራ አመራርን፣

መ/ አንድ ዳይሬክተር በማንኛቸውም ባንክ ሊያገለግል የሚችልበትን ከፍተኛ የሥራ ዘመንና እንደገና ለመመረጥ የሚያበቁትን ሁኔታዎች፣

ሠ/ ለዳይሬክተሮች የሚደረገውን የክፍያ ጣሪያ፣ እና

b) voting right of a holder, who borrowed money from the bank.

2/ Where an influential shareholder of a bank fails to fulfill the prescribed ethical and propriety requirements the National Bank may suspend the voting rights of such person.

PART FOUR
DIRECTORS AND EMPLOYEES OF A BANK

14. Appointment of Directors and Officers

1/ Without prejudice to sub-article (1) of Article 15 of this Proclamation, a director shall be a person with honesty, integrity, diligence and good reputation to the satisfaction of the National Bank.

2/ Appointment of any director, chief executive officer or senior executive officer of a bank at the time of licensing or at any other time may not be valid unless written approval is granted by the National Bank.

3/ The term of office of outgoing directors of a bank may not terminate until written approval for the incoming directors is granted by the National Bank

4/ The National Bank may issue directive on:

a) qualification of competency to be fulfilled by directors;

b) the minimum number of directors in the membership of the board of a bank;

c) the duties, responsibilities and good corporate governance of the boards of directors of bank;

d) the maximum number of years a director may serve in any bank and the conditions for his re-election;

e) the maximum remuneration of directors; and

ረ/ በማናቸውም ባንክ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባልነት ተመርጠው ሊያገለግሉ የሚችሉ የዚያው ባንክ ሠራተኞችን ቁጥር፣ በሚመለከት መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

፲፭. ክልከላ

፩/ ማንኛውም በኢትዮጵያ ውስጥም ሆነ ከኢትዮጵያ ውጭ እምነት በማጉደል ወይም በማጭበርበር ወንጀል ተከስሶ በፍርድ ቤት የጥፋተኝነት ውሳኔ የተሰጠበት ሰው የባንክ ዳይሬክተር ወይም ሠራተኛ መሆን አይችልም።

፪/ ከብሔራዊ ባንክ በቅድሚያ የጽሑፍ ፈቃድ ካልተሰጠው በስተቀር በኢትዮጵያ ውስጥም ሆነ በውጭ አገር በሚገኝ በማናቸውም በፈረሰ ባንክ ዳይሬክተር፣ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ወይም ከፍተኛ ሥራ አስፈጻሚ የነበረ ወይም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በባንኩ ሥራ አመራር የተሳተፈ ሰው በባንክ ዳይሬክተርነት፣ ዋና ሥራ አስፈጻሚነት ወይም ከፍተኛ ሥራ አስፈጻሚነት ወይም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በባንክ ሥራ አመራር መሳተፍ አይችልም።

፫/ የፋይናንስ ድርጅት ዳይሬክተር ወይም ዋና የሥራ አስፈጻሚ በተመሳሳይ ጊዜ የባንክ ዳይሬክተር ሆኖ ሊያገለግል አይችልም። በተጨማሪም ዳይሬክተሩ ወይም ዋና ሥራ አስፈጻሚው አሥር በመቶና ከዚያ በላይ የባለቤትነት ድርሻ የያዘበት የንግድ ድርጅት የባንክ ዳይሬክተር ሆኖ ሊያገለግል አይችልም።

፬/ ማናቸውም የባንክ ሠራተኛ የዚያው ባንክ የዳይሬክተሮች ቦርድ ሊቀመንበር ወይም በማናቸውም ሌላ ባንክ ዳይሬክተር ሆኖ ሊመረጥ አይችልም።

፲፮. ከባንክ ሥራ አመራር ራስን ስለማግለል

ማንኛውም የባንክ ዳይሬክተር ወይም ዋና ሥራ አስፈጻሚ ወይም ከፍተኛ ሥራ አስፈጻሚ ወይም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በባንክ ሥራ መሪነት የሚሳተፍ ሰው፣

፩/ ራሱ ወይም ዳይሬክተር ወይም ሥራ አስፈፃሚ ሆኖ የሚሠራበት ኩባንያ ከስሬአለሁ ብሎ ያመለከተ ወይም በፍርድ ቤት የኪሣራ ውሳኔ የተሰጠበት እንደሆነ ወይም በኪሣራ ምክንያት በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ንብረቱ በቁጥጥር ሥር የዋለበት ወይም ብድር ባለመክፈሉ ምክንያት ንብረቱ በባንክ የተወረሰበት እንደሆነ፣

፪/ የባንክም ሆነ ሌላ ብድር ወይም ታክስ ባለመክፈሉ ተከስሶ የተፈረደበት እንደሆነ፣

f) the maximum number of employees of a bank who may be elected and serve as members in the board of directors of the bank.

15. Prohibitions

1/ No person who has been convicted of any offence involving a breach of trust or a fraud, whether in Ethiopia or elsewhere may be a director or an employee of a bank.

2/ Without prior approval of the National Bank, no person who had been a director, chief executive officer or senior executive officer or otherwise directly or indirectly participated n the management of any bank that wind up, whether in Ethiopia or abroad, may act as a director, chief executive officer or senior executive officer or otherwise be directly or indirectly participate in the management of a bank.

3/ A director or chief executive officer of a financial institution may not, at the same time, serve as a director of a bank. Moreover, a business entity or a company in which such director or chief executive officer has ten percent or more equity interest may not serve as a director of a bank.

4/ An employee of a bank may not be a chairperson of the board of directors of that bank or a director of any other bank.

16. Cessation of Banking Management Functions

Any person who is a director or chief executive officer or senior executive officer or otherwise participate, directly or indirectly, in the management of a bank shall cease to exercise such function if:

1/ he or the company in which he is a director or executive officer, has instituted bankruptcy proceedings or declared bankrupt, or his or the company's assets have been sequestrated because of bankruptcy or been foreclosed by a bank because of failure to repay a loan granted by the bank;

2/ he has been convicted of default on repayments of bank or other credits or tax payment;

፫/ ራሱ ወይም ዳይሬክተር ወይም ሥራ አስፈፃሚ ሆኖ የሚሠራበት ኩባንያ በብሔራዊ ባንክ መመሪያ መሠረት የመከፈያ ጊዜያቸው ላለፈባቸው ብድሮች ለማናቸውም ባንክ ባለዕዳ የሆነ እንደሆነ፣ ወይም

፬/ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የወሰናቸውን የችሎታ መመዘኛዎች ያላሟላ እንደሆነ፣ ራሱን ከባንክ ሥራ አመራር ማግለል አለበት።

፲፯. በብሔራዊ ባንክ ስለሚወሰድ የማገድና የማሰናበት እርምጃ

፩/ ብሔራዊ ባንክ በቂ ነው ብሎ በሚያምንበት ምክንያት ማንኛውንም የባንክ ዳይሬክተር፣ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ወይም ከፍተኛ ሥራ አስፈጻሚ ከሥራ ለማገድ ወይም ለማሰናበት ይችላል።

፪/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ ዓላማ ሲባል "በቂ ምክንያት" የሚከተሉትን ያካትታል፤

ሀ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፭ እና ፲፮ የተደነገጉትን አለማክበር፣

ለ/ በብሔራዊ ባንክ እምነት የባንክ ዳይሬክተር፣ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ወይም ከፍተኛ ሥራ አስፈጻሚ የፈጸመው የፋይናንስ ክፍለ ኢኮኖሚውን መረጋጋት ወይም ጤናማነት፣ ኢኮኖሚውን ወይም የሕዝብን ጥቅም አደጋ ላይ የሚጥል ማንኛውም ድርጊት።

፫/ ብሔራዊ ባንክ የአንድን ባንክ ዳይሬክተሮች ከሥራ በሚያሰናብትበት ጊዜ የዳይሬክተሮቹ ቁጥር በሕግ ከሚፈቀደው በታች ከሆነ ወዲያውኑ የቦርዱን ኃላፊነት ተረክቦ በ፴ ቀናት ውስጥ የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ስብሰባ በመጥራት በተሰናበቱት ዳይሬክተሮች ምትክ ምርጫ እንዲካሄድ ያደርጋል።

፬/ ብሔራዊ ባንክ የአንድን ባንክ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ወይም ከፍተኛ ሥራ አስፈጻሚ ከሥራ ሲያሰናብት፣ የዚያ ባንክ የዳይሬክተሮች ቦርድ በብሔራዊ ባንክ የወጡትን መስፈርቶች የሚያሟላ ሰው ወዲያውኑ መተካት አለበት።

3/ he or the company in which he is a director or executive officer carries non-performing loans, as defined by directives of the National Bank, from any bank; or

4/ he fails to fulfill any of the qualification of competency requirements set by the National Bank.

17. Suspension and Removal by the National Bank

1/ The National Bank may, for sufficient cause, suspend or remove a director, a chief executive officer or a senior executive officer of a bank.

2/ For the purpose of sub-article (1) of this Article, "sufficient cause" shall include the following:

a) failure to comply with the provisions of Article 15 and 16 of this Proclamation;

b) any action detrimental, in the opinion of the National Bank, to the stability or soundness of the financial sector, the economy or the general public interest carried out by a director, a chief executive officer or a senior executive officer a bank.

3/ Where the National Bank removes directors of a bank and as a result of the removal the number of directors falls below the minimum prescribed by the law, it shall immediately assume the powers of the board of directors and shall, within 30 days, call a meeting of shareholders for directors to be elected to replace the removed directors.

4/ Where the National Bank removes the chief executive officer or senior executive officer of a bank, the board of directors of that bank shall fill the vacant post immediately with a person who fulfills the required criteria set by the National Bank.

ክፍል አምስት

የፋይናንስ ግዴታዎችና ገደቦች

፲፰. ተፈላጊውን ካፒታል ስለመያዝ

፩/ ባንኮች መያዝ ያለባቸው አነስተኛ የካፒታል መጠንና መጠባበቂያ እንዲሁም እነዚህ የሚሰሉባቸው ቀመሮች ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

፪/ ብሔራዊ ባንክ ባንኮች ለአደጋ የተጋለጡበትን ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት የተለያዩ የካፒታልና የመጠባበቂያ ግዴታዎችን ለተለያዩ ባንኮች ሊያስቀምጥ ይችላል።

፫/ ብሔራዊ ባንክ የማናቸውም ባንክ ካፒታል ከተወሰነው አነስተኛ መጠን ብታች ነው ብሎ ሲያምን ባንኩ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ሁኔታውን ለማስተካከል የሚያስችሉ እርምጃዎችን እንዲወስድ ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል።

፬/ ማናቸውም ባንክ በካፒታሉ ላይ የደረሰው መሸርሸር መወገዱ በብሔራዊ ባንክ ሳይረጋገጥ የትርፍ ክፍፍል ማድረግ፣ በባለአክሲዮኖች ሂሣብ ውስጥ ማስገባት ወይም መክፈል አይችልም።

፲፱. ሕጋዊ የመጠባበቂያ ሂሣብ ስለመያዝ

፩/ ማናቸውም ባንክ በሂሣብ ዓመቱ መጨረሻ ላይ ካገኘው የተጣራ ትርፍ ቢያንስ ፳፭ በመቶ ወደ ሕጋዊ መጠባበቂያ ሂሣቡ ያዛውራል።

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ ድንጋጌ ቢኖርም፣ መጠባበቂያ ሂሣቡ ከባንኩ ካፒታል ጋር እኩል ሲሆን ከተጣራ ትርፉ በየዓመቱ የሚያዘው የመጠባበቂያ ሂሣብ መጠን ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

፫/ ብሔራዊ ባንክ ሕጋዊ የመጠባበቂያ ሂሣብ ዝቅ የሚደረግባቸውን ሁኔታዎች በመመሪያ ሊወስን ይችላል።

፳. በቂ ገንዘብ-አከል ንብረትና የመጠባበቂያ ሂሣብ ስለመያዝ

፩/ ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት እያንዳንዱ ባንክ በቂ ገንዘብ-አከል ንብረቶችን መያዝ አለበት።

PART FIVE

FINANCIAL OBLIGATIONS AND LIMITATIONS

18. Maintenance of the Required Capital

1/ The minimum amounts of capital and reserves to be maintained by banks and the rules for their computation shall be determined by the directive to be issued by the National Bank.

2/ The National Bank may prescribe different capital and reserve requirements to be maintained by different banks depending on their risk profile.

3/ Where the National Bank considers that the capital of a bank is below the prescribed minimum, it shall require the bank to take, within a specified period of time, measures necessary to rectify the situation.

4/ No bank may at any time declare, credit the account of, or pay to shareholders any dividend until all impairments of its capital, as determined by the National Bank, have been removed.

19. Maintenance of Legal Reserve

1/ Any bank shall, at the end of each financial year, transfer to its legal reserve account a sum of not less than 25 percent of its net profit.

2/ Notwithstanding the provision of sub-article (1) of this Article, when the legal reserve equals the paid-up capital of the bank, the amount to be retained by the bank as a legal reserve from the net profit each year shall be determined by the directive to be issued by the National Bank.

3/ The National Bank may, by directives, specify the circumstances under which the legal reserve account may be reduced.

20. Maintenance of Adequate Liquidity and Reserve Balance

1/ Any bank shall maintain adequate liquid assets in accordance with the directive to be issued by the National Bank.

፪/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ አፈጻጸም "ገንዘብ-አከል ንብረት" ማለት የሚከተሉትን ያጠቃልላል፤

ሀ/ ጥሬ ገንዘብ፣

ለ/ በብሔራዊ ባንክና በብሔራዊ ባንክ ተቀባይነት ባላቸው ሌሎች የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር ባንኮች ያለ ተቀማጭ ገንዘብ፣

ሐ/ በብር ወይም በብሔራዊ ባንክ ተቀባይነት ባለው የውጭ ምንዛሪ የተገለጹና በቀላሉ ወደ ጥሬ ገንዘብ ተቀይረው ወዲያውኑ ተከፋይ ሊሆኑ የሚችሉ ሌሎች ንብረቶች፣

መ/ በብሔራዊ ባንክ በየጊዜው ተቀባይነት አላቸው ተብለው የሚወሰኑ ሌሎች ገንዘብ-አከል ንብረቶች።

፫/ እያንዳንዱ ባንክ ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት በብሔራዊ ባንክ በተከፈተ ሂሣብ መጠባበቂያ በጥሬ ገንዘብ ማስቀመጥ አለበት።

፬/ በዚህ አንቀጽ መሠረት የገንዘብ-አከል ንብረትና የመጠባበቂያ ገንዘብ ሂሣብ ግዴታዎችን ያላሟላ ባንክ ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት መቀጫ ይከፍላል።

፳፩. ፕሮቪ ¡ ንና የእርጅና ቅናሽ የመያዝና ኪሣራ የመሸፈንና የማጣጣት ግዴታዎች

፩/ ማንኛውም ባንክ ለሚከተሉት ጉዳዮች የፕሮቪ ¡ ን ሂሣብ መያዝ አለበት፤

ሀ/ ለብድሮች፣ ቅድሚያ ክፍያዎችና ለማይከፈሉ ወይም አጠራጣሪ ለሆኑ ተሰብሳቢ ሂሳቦች፣

ለ/ ባንኩ የካፒታልና መጠባበቂያ ግዴታዎቹን ማሟላቱን ለማረጋገጥ ስሌት ሲሠራ ከግምት ውስጥ ላልገቡ ዕዳዎችና ሊያጋጥም ለሚችል የዕዳ ተጠያቂነት ሥጋ በዋስትና ለተሰጡና በዋስትናው መሠረት ባንኩ ከሕዝብ ለሚፈለግበት ዕዳ ሊያገለግሉ ለማይችሉ ንብረቶች ዋጋ፣ እና

ሐ/ ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ለሚወሰኑ ሌሎች ጉዳዮች።

2/ For the purpose of sub-article (1) of this Article, "liquid assets" shall include:

a) cash;

b) deposits with the National Bank and other local and foreign banks having acceptance by the National Bank;

c) other assets readily convertible into cash expressed and payable in Birr or foreign currency having acceptance by the National Bank; and

d) such other assets as the National Bank may from time to time declare to be liquid assets.

3/ Any bank shall maintain a cash reserve balance with the National Bank in accordance with the directive to be issued by the National Bank.

4/ Any bank that fails to meet the liquidity and reserve requirements in accordance with this Article shall be subject to a penalty specified by the directive to be issued by the National Bank.

21. Provisioning, Depreciation, Loss Coverage and Amortization Requirements

1/ Provisions shall be made by any bank for the following items:

a) loans, advances and bad or doubtful receivables;

b) the value of any assets lodged or pledged to secure liabilities, including contingent liabilities, that are not included in the calculation made to ascertain the bank's compliance with capital and reserve requirements, where the effect of such lodging and pledging is that such assets are not available for the purpose of meeting the liabilities of the bank to the public; and

c) such other items as the National Bank may prescribe by directive.

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ መሠረት የሚያዘው ፕሮቪ ¡ን መጠንና የሚሰላበት ዘዴ ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

፫/ ማናቸውም ባንክ ለቋሚ ንብረቶች የሚይዘውን የእርጅና ቅናሽ አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ማስላት አለበት።

፬/ ማናቸውም ባንክ የካፒታል ወጪዎችን ቢበዛ በአምስት ዓመት ውስጥ ማጣጣት አለበት።

፭/ ማናቸውም ባንክ በሥራ ሂደት የደረሱና የተጠራቀሙ ኪሣራዎችን በየዓመቱ በሚያገኘው የተጣራ ትርፍ ሙሉ በሙሉ መሸፈን አለበት። እንዲህ ዓይነት ኪሣራዎች ሙሉ በሙሉ እስከሚሸፈኑ ድረስ ባለአክሲዮኖች ትርፍ አይከፋፈሉም።

፮/ ብሔራዊ ባንክ ማናቸውም ባንክ የካፒታልና የመጠባበቂያ ሂሣብ ግዴታዎቹን ማክበሩን ለማረጋገጥ አስፈላጊ የሆነውን ስሌት በሚሠራበት ጊዜ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/፣ /፫/ እና /፬/ መሠረት የተያዘውን ፕሮቪ ¡ንና የቋሚ ንብረቶች የእርጅና ቅናሽ ሂሣብና የተደረገውን የካፒታል ወጪዎች ማጣጣት በቂነት ታሳቢ በማድረግ አስፈላጊውን ማስተካከያ ያደርጋል።

፯/ ማናቸውም ባንክ፣

ሀ/ የባንኩ ማናቸውም ዳይሬክተር ወይም ሠራተኛ በቸልተኝነት ወይም እምነት በማጉደል የሚያደርሰውን እንዲሁም በማናቸውም ባል ተጠበቀ ሁኔታ የሚደርሰውን ኪሣራ ለመሸፈን የሚያስችልና ለዚሁ ጉዳይ ብቻ የተያዘ የመጠኑ በቂነት በብሔራዊ ባንክ የተረጋገጠ ልዩ የመጠባበቂያ ሂሣብ ይይዛል፣ ወይም

ለ/ የዚህ ዓይነቱን ኪሣራ ለመሸፈን ብሔራዊ ባንክ የዋስትና መጠኑን በቂነት እንዲሁም የሁኔታውን አግባብነት በተቀበለው ዓይነት የመድን ውል ይገባል።

፳፪. በአንዳንድ የባንክ አገልግሎቶች ላይ ስለሚጣሉ ገደቦች

፩/ በማናቸውም ባንክ በሚያደርገው ኢንቬስት መንትና በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለማንኛውም ሰው በሚሰጠው ብድር፣ የቅድሚያ ክፍያ ወይም ሌላ የብድር አገልግሎት፣ የገንዘብ ዋስትና ወይም ባንኩ በሚገባቸው ሌሎች ግዴታዎችና ውሎች ላይ የሚጣሉ ገደቦችና ሁኔታዎችን በሚመለከት ብሔራዊ ባንክ መመሪያ ያወጣል።

2/ The amount of provisions to be made pursuant to sub-article (1) of this Article and the manner of calculating the provisions shall be prescribed by directive to be issued by the National Bank.

3/ Any bank shall depreciate its fixed assets in accordance with the relevant law.

4/ Any bank shall amortize its capitalized expenditure within a maximum period of five years.

5/ Any bank shall fully cover its operating and accumulated losses from its annual net profit. No dividend shall be paid to shareholders until such losses are fully covered.

6/ The National Bank shall take into account the adequacy of the provisions, depreciations and amortization stated under sub-articles (1), (3) and (4) of this Article, and make the necessary adjustments, in making the calculations necessary to ascertain that a bank is complying with the provisions concerning capital and reserves.

7/ Any bank shall:

a) either maintain a special reserve account that is, in the opinion of the National Bank, adequate and is reserved exclusively for the purpose of making good any loss resulting from the negligence or dishonesty of any director or employee of the bank and any losses caused by any other unexpected events or circumstances; or

b) insure itself against such losses to an amount and on terms that the National Bank deems adequate.

22. Limitations on Certain Transactions

1/ The conditions and limitations on investments of banks, and a loan, advance or other credit facility, financial guarantee or any other commitment or contracts given by a bank, directly or indirectly to a person shall be determined by directive to be issued by the National Bank.

፪/ ብሔራዊ ባንክ ከወለድ ነፃ የሆነ ተቀማጭ ገንዘብ አሰባሰብና አጠቃቀም ጋር የተያያዙ የባንክ ሥራዎችን ለመቆጣጠር መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

ክፍል ስድስት

ስለፋይናንስ መዝገቦችና ስለውጭ ኦዲት ምርመራ

፳፫. ስለፋይናንስ መዝገቦች

፩/ የዓለም አቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀት ደረጃዎች በየጊዜው ስያሜያቸው ቢለዋወጥም ወይም በሌሎች የሚተኩ ቢሆንም፣ ባንኮች የሂሣብ መግለጫዎቻቸውን በእነዚህ ደረጃዎች መሠረት እንዲያዘጋጁ ብሔራዊ ባንክ ሊያዝ ይችላል።

፪/ ማናቸውም ባንክ፣

ሀ/ የባንኩን ሁኔታ በግልጽና በትክክል በሚያሳይ፣

ለ/ የባንኩን ሥራና የገንዘብ አቋሙን በሚያስረዳ፣ እና

ሐ/ በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎችና ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በወጡ ደንቦችና መመሪያ ዎች መሠረት ሥራውን እያካሄደ ስለመ ሆኑ ብሔራዊ ባንክ ማረጋገጥ በሚያስ ችለው፣

ሁኔታ መዝገቦቹን መያዝ አለበት።

፫/ ማናቸውም ባንክ እያንዳንዱን የሥራ እንቅስቃሴ ዓይነት የሚመዘግብበት የተለየ መዝገብና ሰነዶች መያዝ አለበት። የእነዚህን ሰነዶች አቀራረብና በውስጣቸውም የሚመዘገቡትን ጉዳዮች ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣው መመሪያ ሊወስን ይችላል።

፳፬. ኦዲተሮች ስለመሾም

፩/ ማናቸውም ባንክ የውጭ ኦዲተሮች ይሾ ማል። የኦዲተሮቹ ሹመትም በብሔራዊ ባንክ መጽደቅ አለበት።

፪/ የሚከተሉት ሰዎች የማናቸውም ባንክ የውጭ ኦዲተር ሆነው መሾም አይችሉም፤

ሀ/ የባንኩ ባለአክሲዮን፣ ዳይሬክተር ወይም ሠራተኛ፣

2/ The National Bank may issue directive to regulate banking businesses related to non-interest bearing deposit mobilization and fund utilization.

PART SIX

FINANCIAL RECORDS AND EXTERNAL AUDIT INSPECTION

23. Financial Records

1/ The National Bank may direct banks to prepare financial statements in accordance with the international financial statements standards, whether their designation changes or they are replaced, from time to time.

2/ Any bank shall keep such records as are necessary to:

a) exhibit clearly and correctly the state of its affairs;

b) explain its transactions and financial position; and

c) enable the National Bank to determine whether the bank had complied with the provisions of this Proclamation and regulations and directives issued for the implementation this Proclamation.

3/ Any bank shall register and keep documents for each type of transaction. The form and required entries of such documents may be determined by the directive to be issued by the National Bank.

24. Appointment of Auditors

1/ Any bank shall appoint external auditors. The appointment of such auditors shall be approved by the National Bank.

2/ A person may not be qualified for appointment as an external auditor of a bank if:

a) he is a shareholder, director or employee of that bank;

ለ/ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ተራ ፊደል /ሀ/ የሚሸፈን ሰው የትዳር ጓደኛ ወይም በአንደኛ ደረጃ የሥጋ ወይም የጋብቻ ዘመድ፣

ሐ/ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ተራ ፊደል /ሀ/ ወይም /ለ/ የሚሸፈን ሰው የሥራ ባል ደረባ ወይም ሽሪክ የሆነበት የኦዲት ተቋም።

፫/ የባንኮችን የኦዲት ሥራ ለማካሄድ የሚ ሾሙ የውጭ ኦዲተሮች ማሟላት የሚገባ ቸውን ዝቅተኛ የሥራ ልምድና የዕውቀት ደረጃ ለመወሰን ብሔራዊ ባንክ በየጊዜው መመሪ ያዎችን ሊያወጣ ይችላል።

፬/ ማናቸውም ባንክ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አን ቀጽ /፩/ መሠረት የውጭ ኦዲተር ያል ሾመ እንደሆነ ብሔራዊ ባንክ የውጭ ኦዲ ተር ይሾምለታል።

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፬/ መሠረት ኦዲተር የተሾመለት ማንኛውም ባንክ ለተሾ መው ኦዲተር የሚከፈለውን የአገልግሎት ክፍያ ብሔራዊ ባንክ በሚሰጠው መመሪያ መሠረት መፈጸም አለበት።

፳፭. የኦዲተሮች የሹመት ዘመን

፩/ የባንኮችን የኦዲት ሥራ ለማካሄድ ስለሚ ሾሙ የውጭ ኦዲተሮች የሹመት ዘመን ብሔራዊ ባንክ በየጊዜው መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል።

፪/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፬/፬/ መሠረት በብሔ ራዊ ባንክ የተሾመ የውጭ ኦዲተር የአገልግ ሎት ዘመን እስከ የሚቀጥለው የባንኩ ዓመታዊ የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ ድረስ ይሆናል።

፫/ የማናቸውም ባንክ የውጭ ኦዲተር የተሾ መበት የአገልግሎት ጊዜ ሳያበቃ በማናቸውም ምክንያት ሥራውን ያቋረጠ እንደሆነ፣ ባንኩ ይሽንኑ ሁኔታ ለብሔራዊ ባንክ ወዲያውኑ ማሳወቅ አለበት።

፳፮. የኦዲተሮች ተግባር

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፬ መሠረት የተሾመ የውጭ ኦዲተር ተግባሮች፣ ሌሎች በሕግ የተ ጣሉበት ግዴታዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ባገኙ የኦዲት ደረጃ ዎች መሠረት የባንኩን ሂሣብ መርምሮ ያገኛ ቸውን ውጤቶችና የደረሰባቸውን ድምዳሜ ዎች ለባንኩ ባለአክሲዮኖችና ለብሔራዊ ባንክ ማቅረብ ይሆናል።

b) he or she is a spouse or relative by consanguinity or affinity to the first degree to a person falling within the categories provided under paragraph (a) of this sub-article; or

c) it is a firm of auditors of which any partner or a staff member falls within the categories provided under paragraph (a) or (b) of this sub-article.

3/ The National Bank may issue directives from time to time on the minimum professional experience and knowledge required of external auditors appointed to perform audits of banks.

4/ If a bank fails to appoint an external auditor in accordance with the provisions of sub-article (1) of this Article, the appointment of auditor of such bank shall be made by the National Bank.

5/ Any bank for which an auditor is appointed in accordance with sub-article (4) of this Article shall pay remunerations of the auditor as directed by the National Bank.

25. Tenure of Auditors

1/ The National Bank may issue directives from time to time on tenure of external auditors appointed to perform audits of banks.

2/ An external auditor appointed in accordance with Article 24(4) of this Proclamation shall hold office until the next annual general meeting of the shareholders of the bank.

3/ Any bank the external auditor of which, for any reason, terminates his service before his term of office shall forthwith notify such fact to the National Bank.

26. Duties of Auditors

1/ Without prejudice to the duties imposed by other relevant laws, the duty of the external auditor, appointed in accordance with the provisions of Article 24 of this Proclamation shall be to report its audit findings and conclusions, carried out on the basis of international auditing standards, to the shareholders of the bank and the National Bank.

፪/ ብሔራዊ ባንክ በውጭ አዲተሮች የሚሠራውን የአዲት ሥራ ጥልቀትና ሽፋንን በሚመለከት ተጨማሪ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

፫/ በማናቸውም ባንክ የውጭ አዲተር ሆኖ የተሾመ ሰው፣ በመደበኛ የሥራ ሂደትና ለሌላ ለማንኛውም ሰው ከሚሰጠው አገልግሎት ባል ተለየ ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር፣ በዚያው ባንክ ሂሣብ መያዝ ወይም ከባንኩ ማናቸውንም ዓይነት ብድር፣ የቅድሚያ ክፍያ ወይም ሌላ አገልግሎት ማግኘት አይችልም።

2/ The National Bank may further issue directive as to the depth and coverage of the audit to be performed by external auditors.

3/ A person appointed as an auditor of a bank may not operate an account with, or be granted any type of loan, advance or facility from, that bank except in the normal course of business and at an arm's length basis.

፳፯. የአዲት ሪፖርት

27. Audit Reports

፩/ ብሔራዊ ባንክ የአንድ ባንክ የሂሣብ ዓመት ከተጠናቀቀ በኋላ በምን ያህል ጊዜ የአዲት ሪፖርት መውጣት እንዳለበት በመመሪያ ይወስናል።

1/ The National Bank shall determine by directive the time limit for issuance of audit reports after the end of a bank's financial year.

፪/ የማንኛውም ባንክ አዲተር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ የተመረመሩትን የሂሣብ መግለጫዎች እንዲሁም የአዲት ግኝትና አስተያየት ያካተተ ሙሉ የአዲት ሪፖርት ለብሔራዊ ባንክ ማቅረብ አለበት።

2/ The auditor of any bank shall submit to the National Bank a complete audit report, including audit findings and recommendations, within the time limit set in accordance with sub-article (1) of this Article.

፫/ ብሔራዊ ባንክ የቀረበውን የአዲት ሪፖርት ካላመነበት ድጋሚ የሂሣብ ምርመራ እንዲካሄድ ማዘዝ ወይም ሌላ የውጭ አዲተር በመሾም ሂሣቡ እንደገና እንዲመረመር ማድረግ ይችላል። ባንኩ በብሔራዊ ባንክ በሚሰጠው መመሪያ መሠረት አዲስ የተሾመውን የውጭ አዲተር የአገልግሎት ክፍያ መሸፈን አለበት።

3/ The National Bank may, if not satisfied with the external audit report, order a second audit or require the prompt appointment of a new auditor who shall make an independent audit report. The remunerations of the newly appointed auditor shall be paid by the bank as directed by the National Bank.

፬/ የማንኛውም ባንክ የውጭ አዲተር የሂሣብ ምርመራ ተግባሩን በሚያካሂድበት ጊዜ፣

ሀ/ የዚህ አዋጅ፣ የሌሎች አግባብ ያላቸው ሕጎች ወይም በዚህ አዋጅ መሠረት የወጡ ደንቦች ወይም መመሪያዎች ድንጋጌዎች በከፍተኛ ደረጃ መጣሳቸውን ወይም ያለመከበራቸውን፣

ለ/ በባንኩ ወይም በማናቸውም የባንኩ ዳይሬክተር ወይም ሠራተኛ የማጭበርበር ወይም ሌላ የእምነት ማጉደል ወንጀል መፈጸሙን፣

ሐ/ የባንኩን ካፒታል ፳፭ በመቶ ወይም ከዚያ በላይ በሆነ መጠን የሚቀንስ ኪሣራ የደረሰ መሆኑን፣

4/ Where the external auditor of any bank, in the course of the performance of his audit duties, finds out that:

a) there has been a serious breach of, or non-compliance with, the provisions of this Proclamation, other relevant laws or regulations or directives issued in accordance with this Proclamation;

b) a criminal offence involving fraud or other dishonesty has been committed by the bank or any of its directors or employees;

c) losses have been occurred which reduce the total capital of the bank by 25% or more;

መ/ ባንኩ እንደቀጣይ ድርጅት ሥራውን ለማካሄድ ያለውን አቅም የሚነዳ ወይም የገንዘብ አስቀማጮችን ወይም የገንዘብ ጠያቂዎችን ጥቅም አደጋ ላይ የሚጥል ከባድ የሆነ የአሠራር ጉድለት የተከሰተ መሆኑን፣ ወይም

ሠ/ ሌሎች ከባድ የአሠራር ጉድለቶች ወይም ጥፋቶች ተከስተው መገኘታቸውን፣

ሲደርስበት ጉዳዩን ለብሔራዊ ባንክና ለሌሎች ለሚመለከታቸው አካላት ወዲያውኑ ማሳወቅ አለበት።

፭/ ብሔራዊ ባንክ ማንኛውንም የባንክ የውጭ ኦዲተር ኦዲት የሚያደርገውን ባንክ የተመለከቱ ጉዳዮች ላይ በማንኛውም ጊዜ ጠርቶ ውይይት ሊያካሂድ ይችላል።

ክፍል ሰባት
መረጃ ስለመስጠትና በባንኮች ላይ ስለሚካሄድ ቁጥጥር

፳፰. መረጃ ስለመስጠት

፩/ ማናቸውም ባንክ ብሔራዊ ባንክ በሚወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ በሚገባ የተፈረሙ የፋይናንስ መግለጫዎችንና ሌሎች በብሔራዊ ባንክ የሚወሰኑ ሪፖርቶችን ለብሔራዊ ባንክ ማቅረብ አለበት።

፪/ ማናቸውም ባንክ፣

ሀ/ በኦዲተር የተመረመረና የሥራ እንቅስቃሴውን የሚያሳይ የሂሣብ ሚዛንና የትርፍና ኪሣራ መግለጫዎችን በሁሉም የባንኩ የሥራ ቦታዎችና ቅርንጫፎች ግልጽ በሆነ ቦታ ዓመቱን ሙሉ እንዲታዩ ማድረግ አለበት፣

ለ/ የሂሣብ ሚዛን እንዲሁም የትርፍና ኪሣራ መግለጫ ማብራሪያ ጽሑፎችን አባሪ በማድረግ ሰፊ ስርጭት ባለው ጋዜጣ ላይ አሳትሞ ያወጣል፣

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፪/ መሠረት የፋይናንስ መግለጫዎችን ለሕዝብ እይታ ዝግጁ የማድረጉና በጋዜጣ አሳትሞ የማውጣቱ ተግባር የባለአክሲዮኖች ዓመታዊ ጉባኤ በተካሄደ በሁለት ሣምንታት ውስጥ መፈጸም አለበት።

፬/ ብሔራዊ ባንክ አግባብ አላቸው ብሎ የሚያምንባቸውን መረጃዎች ከባንኮች መጠየቅና ማግኘት ይችላል፣ ሆኖም

d) serious irregularities have occurred which may jeopardize the bank's ability to continue conducting its business or the security of its depositors or creditors; or

e) any other grave irregularities or offences have occurred;

he shall immediately report the matter to the National Bank and other concerned bodies.

5/ The National Bank may call at any time the external auditor of a bank to discuss issues related to the bank being audited by the auditor.

PART SEVEN
DISCLOSURE OF INFORMATION AND INSPECTION OF BANKS

28. Disclosure of Information

1/ Every bank shall, within a time period to be determined by the National Bank, send to the National Bank duly signed financial statements and other reports as prescribed by it.

2/ Every bank shall:

a) exhibit at every place of its business, including its branches, in a conspicuous place throughout the year, a copy of the last audited balance sheet and profit and loss account in respect of all of its operations;

b) cause such balance sheet and profit and loss account, together with the notes thereto, to be published in a newspaper of wide circulation.

3/ The exhibition and publishing of financial statements pursuant to sub-article (2) of this Article shall occur within two weeks after the annual shareholders' meeting.

4/ The National Bank may collect any information from banks, as it may deem appropriate. Provided, however, that such information may not be disclosed to any person unless the disclosure:

ሀ/ የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎችን ለማስፈጸም ሲባል፣

ለ/ የባንኮችን የፋይናንስ ጤናማነት ለማረጋገጥ፣

ሐ/ በሕግ ለተፈቀደላቸው ሰዎች፣

መ/ ብሔራዊ ባንኩ ተጠሪ ለሆነለት አካል፣

ሠ/ በፍርድ ቤት በመታዘዙ፣ ወይም

ረ/ ኢትዮጵያ የገባችባቸውን ዓለም አቀፍ ግዴታዎች ለመወጣት ሲባል፣

ካልሆነ በቀር እነዚህ መረጃዎች ለማንኛውም ሰው ተላልፈው አይሰጡም።

፫/ የማናቸውም ባንክ የዳይሬክተሮች ቦርድ የሚከተሉት ሁኔታዎች በባንኩ ሲከሠቱ ወይም ሊከሰቱ ይችላሉ ብሎ ሲገምት ሁኔታውን በጋራም ሆነ በተናጠል ወዲያውኑ ለብሔራዊ ባንክ ማሳወቅ አለበት፤

ሀ/ ለገንዘብ አስቀማጮችና ለሌሎች አበዳሪዎች ያለበትን ግዴታ መወጣት የማይችል ሲሆን፣ ወይም

ለ/ ለገንዘብ አስቀማጮች ወይም ለሌሎች አበዳሪዎች ክፍያዎችን በወቅቱ ለመፈጸም ሊሳነው የሚችል ከሆነ።

a) is made for the purpose of fulfilling the requirements of this Proclamation;

b) is required to ensure the financial soundness of banks;

c) is made to recipients who are legally authorized to obtain such information;

d) is made to the body to which the National Bank is accountable;

e) is ordered by a court; or

f) is required for the purpose of meeting obligations which Ethiopia entered into under international agreements.

5/ The Board of directors of a bank shall, jointly or severally, immediately report in writing to the National Bank where the following happened or likely to happen that the bank:

a) cannot meet its obligations to its depositors or other creditors; or

b) possibly unable to made payments on time to depositors or other creditors.

፳፱. <u>በባንኮች ላይ ስለሚካሄድ ቁጥጥር</u>

፩/ ብሔራዊ ባንክ በየጊዜው ወይም በማናቸውም ጊዜ ያለቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በማናቸውም ባንክ ላይ በቦታው ተገኝቶ ቁጥጥር ማካሄድ ወይም እንዲካሄድ ማድረግ ይችላል።

፪/ ከጠቅላላው ገንዘብ አስቀማጮች በቁጥር አንድ አምስተኛ ወይም በባንኩ ዘንድ ካለው ጠቅላላ ገንዘብ ውስጥ አንድ ሦስተኛ አስቀማጭ የሆኑ አመልካቾች በአንድ ባንክ ላይ ቁጥጥር ማካሄድ አስፈላጊ መሆኑን የሚያስረዳ መረጃ አያይዘው ጥያቄ ካቀረቡ፣ ብሔራዊ ባንክ ማመልከቻ የቀረበበት ባንክ በጤናማ ሁኔታ መገኘቱንና የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች እንዲሁም በዚህ አዋጅ መሠረት የወጡ ደንቦችና መመሪያዎች የባንኩን የሥራ እንቅስቃሴ በመምራት ሂደት ውስጥ መከበራቸውን ለማረጋገጥ በሚስጥር ቁጥጥር ማካሄድ ወይም እንዲካሄድ ለማድረግ ይችላል።

29. <u>Inspection of Banks</u>

1/ The National Bank may, periodically or at any time, without prior notice, make, or cause to be made, an on-site inspection of any bank.

2/ Where an application, accompanied with supporting evidence, is made to the National Bank by one-fifth of the total number of depositors or by any number of depositors holding not less than one-third of the deposits of a bank, the National Bank shall examine, or cause to be examined, under conditions of secrecy, the affairs of the bank in order to determine whether it is in a sound condition and the provisions of this Proclamation and regulations and directives issued pursuant to this Proclamation have been complied with.

፫/ በባንኮች ላይ የሚካሄድ የቁጥጥር ሥራ በአንድ ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ በብሔራዊ ባንክ ባለሥልጣኖች ወይም ለዚህ ዓላማ ሲባል ብሔራዊ ባንክ በሚቀጥራቸው ሌሎች እምነት በሚጣልባቸውና ብቃት ባላቸው ሰዎች ሊካሄድ ይችላል።

፬/ ብሔራዊ ባንክ ቁጥጥር እንዲያካሂዱ የሚመ ድባቸው ሰዎች ቁጥጥሩን በሚገባ ለመፈጸም የሚያስችሏቸው የባንኩን መዝገቦችና አሠራ ሮች የሚመለከቱ መረጃዎችና መግለጫዎች የባንኩ ሠራተኞች እንዲሰጧቸው የመጠየቅ ሥልጣን ይኖራ ቸዋል።

፭/ በባንክ ቁጥጥር ሥራ ሂደት የተሰበሰቡ መረጃዎች ቁጥጥሩን ባካሄዱት ሰዎች በምስጢር መጠበቅ አለባቸው።

፴. የቁጥጥር ሪፖርት

፩/ የቁጥጥሩ የመጨረሻው ሪፖርት ከመዘጋ ጀቱ በፊት ለተመርማሪው ባንክ እንዲደር ሰው ተደርጎ በሪፖርቱ ላይ አስተያየቱን እንዲያቀርብ ዕድል ይሰጠዋል።

፪/ ለብሔራዊ ባንክ የቀረበው የቁጥጥር ሪፖርት ይዘት፣

ሀ/ ቁጥጥሩን ባካሄዱት ሰዎች እንዲሁም ቁጥጥሩ በተደረገበት ባንክ ዳይሬክ ተሮችና ሠራተኞች፣ እና

ለ/ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎችን ለማስፈ ጸም ወይም የሕዝብን ጥቅም ለማስ ከበር ሲባል ካልሆነ በቀር በብሔራዊ ባንክ፣ በምስጢር መጠበቅ አለበት።

፴፩. የማስተካከያ እርምጃዎች

በተደረገው ቁጥጥር ተመርማሪው ባንክ አግባብ ያላቸው ሕጎችና መመሪያዎችን ያልተከተለ ወይም በተሰጠው የባንክ ሥራ ፈቃድ የተመለከቱትን ግዴታዎች ያልፈጸመ መሆኑ፣ የባንዘብ አስቀማጮችን ጥቅም በሚጎዳ ማናቸውም ተግባር ላይ ተሠማርቶ ማገኘቱ ወይም በባንኩ ሥራ አመራር ላይ ከባድ ድክመት የተከሰተ መሆኑ የተረጋገጠ እንደሆነ ብሔራዊ ባንክ፣

፩/ ከቁጥጥሩ የሚነሱ ወይም የተያያዙ ማናቸ ውንም ጉዳዮች በሚመለከት ለመነጋገር የባለአክሲዮኖች ወይም የዲሬክተሮች ቦርድ ስብሰባ እንዲጠራ ወይም የዚህ ባንክ የሥራ ኃላፊዎች ምርመራውን በሚመለከት የብሔራዊ ባንክ ኃላፊዎችን እንዲያነጋግሩ ለማዘዝ፣

3/ Inspection of banks may be carried out by one or more officers of the National Bank or by trustworthy and qualified persons employed by the National Bank for this purpose.

4/ Persons assigned by the National Bank to inspect any bank shall be authorized to request from the personnel of the inspected bank such information and explanation on the records and transactions of the inspected bank that are necessary for the effectiveness of carrying out the inspection.

5/ The information gathered in the course of the inspection of any bank shall be considered confidential by the persons carrying out the inspection.

30. Inspection Report

1/ The inspection report before its final preparation shall be communicated to the inspected bank and, the inspected bank shall be given an opportunity to express its views on the report.

2/ The content of the inspection report submitted to the National Bank shall be considered as confidential by:

a) the persons carrying out the inspection, and the directors and employees of the inspected bank; and

b). the National Bank, unless it is for the purpose of fulfilling the requirements of this Proclamation or to the interest of the public;

31. Corrective Measures

Where an inspection of a bank results in a finding that the bank has failed to comply with the relevant laws and directives or with the terms and conditions of license or has engaged in practices detrimental to the interests of depositors or has serious weaknesses in its corporate governance, the National Bank may:

1/ require the bank to call a meeting of its shareholders or board of directors for the purpose of considering any matter arising out of or relating to the inspection or require officers of the bank to discuss any such matter with officers of the National Bank;

፪/ አንድ ወይም ከዚያ በላይ ኃላፊዎቹን በባንኩ የዳይሬክተሮች ቦርድ ወይም በቦርዱ በተሰየመ ማናቸውም ኮሚቴ ወይም ሌላ አካል ስብሰባ ላይ እንዲገኙ ለመወከልና አስተያየታቸው በስብሰባዎቹ ላይ እንዲሰማ ለማድረግ፣

፫/ ባንኩ ሊወስድ የሚገባውን የማስተካከያ እርምጃ እንዲወስድ በጽሑፍ ለማዘዝ፣

፬/ የባንኩን አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ ዳይሬክተሮች፣ ዋና የሥራ አስፈጻሚ ወይም ከፍተኛ የሥራ አስፈጻሚዎች ከሥራ ለማገድ ወይም ለማሰናበት ወይም ለዚሁ ሲባል ባወጣቸው መመሪያዎች መሠረት በነዚሁ ላይ የገንዘብ መቀጫ ለመወሰን፣

፭/ ባንኩ አዲስ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶችን እንዳይከፍት ለመከልከል፣

፮/ የባንኩን የአክሲዮን ትርፍ ድርሻ ክፍፍል ለመገደብ፣ ለማዘግየት ወይም ለመከል ከል፣

፯/ ባንኩ ለተወሰነ ጊዜ በከፊልም ሆነ በሙሉ የባንክ ሥራ እንዳይሠራ ለማዘዝ፣ ወይም

፰/ ባንኩ በሞግዚት አስተዳደር ሥር እንዲ ሆን ለማድረግ፣

ይችላል።

ክፍል ስምንት
ፈቃድ ስለመሠረዝ፣ ስለሞግዚት አስተዳደርና ስለመፍረስ

፴፪. ፈቃድ ስለመሠረዝ

፩/ ብሔራዊ ባንክ በሚከተሉት ምክንያቶች የማናቸውንም ባንክ ፈቃድ ወዲያውኑ ሊሰርዝ ይችላል፣

ሀ/ የባንኩ ፈቃድ የተሰጠው በሀሰት ወይም በተሳሳተ መረጃ ላይ ተመሥርቶ መሆኑ ሲረጋገጥ፣ ወይም

ለ/ ባንኩ ፈቃዱ በተሰጠው በ፲፪ ወራት ውስጥ ሥራውን ያልጀመረ እንደሆነ፣

፪/ ብሔራዊ ባንክ የማናቸውንም ባንክ ፈቃድ እንዲሰረዝ ሲወስን ፈቃዱ የተሰረዘበት ባንክ ዋና መሥሪያ ቤት በሚገኝበት አካባቢ በሰፊው በሚሠራጭ ጋዜጣ ውሳኔውን አሳትሞ ያወጣል።

2/ assign one or more of its officers to watch the proceedings at any meeting of the shareholders, board of directors or any committee or any other body constituted by the board of the bank, and require the bank to give an opportunity to the officers to be heard at such meetings;

3/ instruct in writing corrective measures to be taken by the bank;

4/ order the dismissal or suspension of one or more directors, the chief executive officer or senior executive officers of the bank, or impose fines on such persons in accordance with its directives prescribed for such purpose;

5/ prohibit the bank from opening new branch offices;

6/ restrict, suspend or prohibit payment of dividends by the bank;

7/ order the bank to suspend for specified time any or all of its banking businesses; or

8/ put the bank under receivership.

PART EIGHT
REVOCATION OF LICENSE, RECEIVERSHIP AND LIQUIDATION

32. Revocation of License

1/ The National Bank may revoke the license of any bank immediately if:

a) it is confirmed that the licensing of the bank was made on the basis of false or wrong information; or

b) the bank has failed to commence operations within 12 months following the grant of the license.

2/ The decision to revoke the license of a bank shall be published by the National Bank in a newspaper of wide circulation at the place where the head office of the bank is situated.

፫/ ፈቃድ የመሰረዝ ውሳኔ በጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ወይም ብሔራዊ ባንክ ከሚወስነው ማናቸውም ሌላ ቀን ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል።

፬/ ፈቃዱ የተሰረዘበት ባንክ የፈቃድ ስረዛው ውሳኔ ተፈጻሚ ከሆነበት ቀን ጀምሮ ማናቸውንም ዓይነት የባንክ ሥራ መሥራት አይችልም።

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩//ለ/ መሠረት ብሔራዊ ባንክ ፈቃድ ለመሰረዝ በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ማንኛውም ሰው የፈቃድ ስረዛው ውሳኔ ተፈጻሚ ከሆነበት ቀን ጀምሮ በ፴ ቀናት ውስጥ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሊያመለክት ይችላል።

3/ The revocation of license shall become effective on the date of its publication or on any other date as the National Bank may specify.

4/ Any bank shall be prohibited from engaging in any banking business starting from the effective date of the revocation of its banking license.

5/ Any person aggrieved by the decision of the National Bank to revoke the license in accordance with sub-article (1)(b) of this Article may petition to the Federal High Court within 30 days from the effective date of the revocation.

፴፫. ሞግዚት ስለመሾም

፩/ ብሔራዊ ባንክ ከሚከተሉት አንዱ ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ሁኔታዎች በአንድ ባንክ መኖራቸውን ሲያምን ባንኩን ተረክቦ የሚቆጣጠር ሞግዚት ይሾማል፤

ሀ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፪ ንዑስ አንቀጽ ፩/ሀ/ መሠረት የባንኩ ፈቃድ የተሰረዘ ከሆነ፣

ለ/ ባንኩ ዕዳ መክፈል የማይችልበት ወሰን የደረሰ ከሆነ፣

ሐ/ ሕግን ወይም መመሪያን በመተላለፍ ወይም ጥንቃቄ በጎደለው አሰራር ምክንያት በቀላሉ የማይገመት የሀብት ወይም የገቢ ብክነት የተከሰተ እንደሆነ፣

መ/ ባንኩ ሥራውን እየካሄደ ያለው የገንዘብ አስቀማጮችን ጥቅም አደጋ ላይ ሊጥል በሚችል ጤናማ ባልሆነና ጥንቃቄ በጎደለው የአሰራር ሁኔታ ከሆነ፣

ሠ/ በብሔራዊ ባንክ የተጣለውን ማናቸውንም ገደብ ባንኩ ሆነ ብሎ የጣሰ ከሆነ፣

ረ/ ባንኩ የሂሳብ መዝገቦችን፣ ሰነዶችን ወይም ሪኮርዶችን ሥልጣን ለተሰጠው የብሔራዊ ባንክ ተቆጣጣሪ ወይም ወኪል ለቁጥጥር ተግባር ለማቅረብ እምቢተኛ የሆነ እንደሆነ፣

33. Appointment of Receiver

1/ The National Bank shall appoint a receiver to take possession and control of a bank if it determines that one or more of the following circumstances exist in respect of the bank:

a) the license of the bank is revoked as stipulated under sub-article 1(a) of Article 32 of this Proclamation;

b) the bank has become insolvent;

c) there is a substantial dissipation of assets or earnings due to a violation of any law or directives or due to and unsound practice;

d) the bank has engaged in a pattern of unsafe and unsound practices which may likely constitute a significant danger to its depositors;

e) the bank intentionally violated any of the limitations imposed by the National Bank;

f) the bank refuses to submit its books of accounts, documents or records for inspection to any authorized inspector or agent of the National Bank;

ሰ/ ባንኩ በመደበኛ የሥራ ሂደት ግዴታ ዎቹን ለመወጣት ወይም የባንዘብ አስቀማጮችን ጥያቄ ለማሟላት አይ ችልም የሚል ጠንካራ ግምት ሊኖር ከቻለ፣

ሸ/ ባንኩ ካፒታሉን በሙሉ ወይም የካፒ ታሉን አብዛኛውን ክፍል የሚያመ ናምን ኪሳራ የደረሰበት ወይም እንደ ሚደርስበት የሚገመት ከሆነ፣

ቀ/ ባንኩ በብሔራዊ ባንክ የተወሰነውን አነስተኛ የካፒታል መጠን የማያሟላ ከሆነ፣

በ/ ባንኩ በቂ ካፒታል የሌለውና ወደፊ ትም ካፒታሉን በሚያስፈልገው መጠን ለመጨመር አቅም እንደማይኖረው የሚገመት ከሆነ፣

ተ/ ባንኩ በብሔራዊ ባንክ ሲታዘዝ ካፒታ ሉን በሚያስፈልገው በቂ መጠን መጨ መር ያልቻለ እንደሆነ ወይም ብሔራዊ ባንክ በሚወስነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ካፒታሉን መልሶ ለመገንባት የሚያስችል ተቀባይነት ያለው ዕቅድ ያላቀረበ እንደሆነ፣

ቸ/ ባንኩ ለብሔራዊ ባንክ ቀርቦ ተቀባይ ነት ያገኘ ካፒታልን መልሶ የመገን ባት ዕቅድ ተግባራዊ ማድረግ ያልቻለ እንደሆነ፣

ነ/ ባንኩ ተገቢ ያልሆነ፣ ሕገወጥ ወይም ጥንቃቄ የጎደላቸው ተግባሮችን በማ ከናወን የሃገሪቱን ወይም የሕዝቡን አጠቃላይ የኢኮኖሚ ጥቅም አደጋ ላይ የሚጥሉ ፖሊሲዎች የተከተለ ከሆነ፣

ኘ/ ከብሔራዊ ባንክ በቅድሚያ በጽሑፍ ፈቃድ ሳያገኝ ከሌላ ባንክ ጋር የተቀላቀለ እንደሆነ፣

አ/ በብሔራዊ ባንክ የወጡትን መስፈር ቶች የሚያሟሉ ዳይሬክተሮችን፣ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ወይም ከፍተኛ ሥራ አስፈጻሚዎችን መሾም ያልቻለ እንደ ሆነ፣

ከ/ በባለአክሲዮኖች ውሳኔ ባንኩ በሞግ ዚት አስተዳደር ሥር እንዲሆን ከተጠ የቀ ወይም ከብሔራዊ ባንክ በቅድ ሚያ ፈቃድ በማግኘት የባንኩ ባለሀ ብቶች ባንኩን ለማፍረስ የወሰኑ እንደ ሆነ፣ ወይም

g) there is a strong likelihood that the bank may be unable to fulfill its obligations or meet its depositors' demands in the normal course of business;

h) the bank has incurred, or is likely to incur, losses that will deplete all or substantial part of its capital;

i) the bank does not meet the minimum capital requirement set by the National Bank;

j) the bank is undercapitalized and has no reasonable prospect of becoming adequately capitalized;

k) the bank fails to become adequately capitalized when required to do so by the National Bank or fails to submit a capital restoration plan acceptable to the National Bank within the time prescribed by the National Bank; or

l) the bank fails to implement a capital restoration plan submitted to and accepted by the National Bank;

m) the bank follows policies which would endanger the general economic interest of the country or the public through inappropriate, illegal or imprudent banking practices;

n) the bank is merged with another bank without the prior written authorization of the National Bank;

o) the bank fails to appoint directors, chief executive officer or senior executive officers that fulfill the requirements set by the National Bank;

p) the bank, by the resolution of its shareholders, has requested to be put under receivership, or the owners of the bank have decided, subject to the prior approval of the National Bank, to liquidate the bank; or

ወ/ ባንኩ እንደ አንድ ራሱን ችሎ የሚን ቀሳቀስ ሕጋዊ ተቋም መቀጠል የተ ሳነው እንደሆነ።

ፎ/ ብሔራዊ ባንክ ለአንድ ባንክ ሞግዚት መሾሙን፣ ለሹመቱ ምክንያት የሆነውን ጉዳይ፣ የሞግዚቱን ስም፣ ሹመቱ የሚፀ ናበትን ቀንና ማናቸውንም ሌሎች አግባብ ያላቸውን መረጃዎች በመጥቀስ በሰፊው በሚሰራጭ ጋዜጣ ላይ አሳትሞ ያወጣል።

ቮ/ በዚህ አንቀጽ መሠረት የተሾመ ማንኛ ውም ሞግዚት ተጠሪነቱ ለብሔራዊ ባንክ ይሆናል።

ፀ/ ብሔራዊ ባንክ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው እራሱ በሞግዚትነት ሊሰራ ይችላል።

፴፬. <u>ለሞግዚትነት የሚያበቁ መስፈርቶች</u>

፩/ በብሔራዊ ባንክ የሚሾም ማንኛውም ሞግዚት በብሔራዊ ባንክ አስተያየት ከፍተኛ የሙያ ብቃትና ታማኝነት ያለው ሰው መሆን አለበት።

፪/ ሞግዚቱ የንግድ ድርጅት በሚሆንበት ጊዜ፤

ሀ/ የሞግዚት አስተዳደሩን በበላይነት የሚመራው ኃላፊ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ የተመለከተውን መስፈ ርት ማሟላት፣ እና

ለ/ ድርጅቱ የመልካም ሥራ አፈጻጸም ዋስትና ከታወቀ የመድን ኩባንያ ወይም ባንክ ማቅረብ፣

አለበት።

፫/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ እና /፪/ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ ማንኛ ውም በሞግዚትነት የሚሾም ሰው ብሔ ራዊ ባንክ የሚያወጣቸውን ሌሎች ተጨ ማሪ መስፈርቶች ማሟላት አለበት።

፴፭. <u>የሞግዚት የአገልግሎት ክፍያዎች</u>

፩/ ለሞግዚት የሚፈጸም የአገልግሎት ክፍያ መጠን በብሔራዊ ባንክ ይወሰናል።

፪/ የሞግዚት የአገልግሎት ክፍያ በሞግዚት አስተዳደሩ ሥር በሆነው ባንክ እጅ በሚገኝ ገንዘብ ወይም በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት የባንኩ ንብረት ተሸጦ በሚገኝ ገቢ ይሸፈናል።

q) the bank has ceased to operate as a legally independent entity.

2/ The appointment of a receiver shall be published by the National Bank in newspapers of wide circulation, indicating the reason for appointment, the name of the receiver, the effective date and any other relevant information.

3/ A receiver appointed pursuant to this Article shall be accountable to the National Bank.

4/ The National Bank may act as a receiver if it finds necessary.

34. <u>Qualifications of Receiver</u>

1/ Any receiver to be appointed by the National Bank shall, in the opinion of the National Bank, be of the highest professional qualifications and personal integrity.

2/ Where the receiver is a corporate entity:

a) the principal officer in charge of the receivership shall meet the qualification requirements stipulated under sub-article (1) of this Article; and

b) the corporate entity shall provide adequate performance guarantee from a reputable insurance company or bank.

3/ Without prejudice to the provisions of sub-articles (1) and (2) of this Article, any person to be appointed as receiver shall meet such other additional requirements as may be specified by the National Bank.

35. <u>Remunerations of Receiver</u>

1/ The amount of remunerations for services of a receiver shall be determined by the National Bank.

2/ The remuneration of a receiver shall be paid either from funds available with the bank being placed under receivership or from the proceeds of liquidation pursuant to the provisions of this Proclamation.

፴፮. የሞግዚትነት አስተዳደር የሚቆይበት ጊዜ

፩/ ብሔራዊ ባንክ የማንኛውም ባንክ የሞግዚትነት አስተዳደር የሚቆይበትን ጊዜ ይወስናል።

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ ድንጋጌ ቢኖርም፣ ብሔራዊ ባንክ ማንኛውም የባንክ ሞግዚት የተጣለበትን ኃላፊነት አጥጋቢ በሆነ መንገድ አልተወጣም ብሎ ሲያምን በማናቸውም ጊዜ ከሥራ ሊያሰናብተው ይችላል።

፫/ ብሔራዊ ባንክ የሞግዚት አስተዳደር የሥራ ጊዜ እንደተጠናቀቀ ወይም ሞግዚቱ ከሥራ እንደተሰናበተ ወዲያውኑ ይህንኑ በሰፊው በሚሰራጭ ጋዜጣ አሳትሞ ያወጣል።

፴፯. የሞግዚት አስተዳደር ስር መዋል የሚያስከትለው ውጤት

ማንኛውም ባንክ ሞግዚት እንደተሾመለት ብሔራዊ ባንክ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፫/፪/ መሠረት በጋዜጣ እንዳስታወቀ፣

፩/ ከሞግዚቱ ቅድሚያ ፈቃድ ካልተገኘ በስተቀር በሞግዚት አስተዳደር ሥር በዋለው ባንክ ስም ምንም ዓይነት እርምጃ ሊወሰድ አይችልም፣

፪/ የባለአክሲዮኖች፣ የዳይሬክተሮችና የሌሎች የባንኩ የሥራ ኃላፊዎች ሥልጣን ታግዶ ለሞግዚቱ ይተላለፋል፣

፫/ የባንኩ መብትና ሥልጣን እንዲሁም ማንኛውም ገንዘብ አስቀማጭ ወይም አበዳሪ በባንኩ ወይም በባንኩ ንብረቶች ላይ ያለው መብትና ሥልጣን ወዲያውኑ ወደ ሞግዚቱ ይተላለፋሉ፣

፬/ ሞግዚቱ የባንኩን ንብረቶችና መዛግብት በሙሉ ተረክቦ ባለአክሲዮኖች፣ ዳይሬክተሮችና ከፍተኛ ሥራ አስፈጻሚዎች በነበራቸው ሥልጣን መሠረት ባንኩን ያስተዳድራል፣ የባንኩንም ሥራ አጠቃሎ ይሰራል፣

፭/ የባንኩን የክፍያ ጥያቄ ወይም መብት በይርጋ ሊያሳግድና ሊያስቀር የሚችል ማንኛውም በሕግ፣ በውል ወይም በሌላ ሁኔታ የተወሰነ የጊዜ ገደብ ከሚያበቃበት ጊዜ ጀምሮ ለስድስት ወራት ይራዘማል፣

፮/ ማናቸውም በባንኩ ንብረትና ሀብት ላይ የተጣለ የፍርድ ቤት እግድ ወይም በባንኩ የተሰጠ ዋስትና ይሻራል፣ እንዲሁም ባንኩ በሞግዚት አስተዳደሩ ሥር በሚቆይበት ጊዜ ሁሉ በባንኩ ንብረት ላይ አዲስ የፍርድ ቤት እግድ ሊተላለፍ ወይም ዋስትና ሊሰጥ አይችልም፣ ሆኖም ይህ ድንጋጌ፤

36. Duration of Receivership

1/ The duration of receivership of any bank shall be determined by the National Bank.

2/ Notwithstanding the provisions of sub-article (1) of this Article, the National Bank may, at any time, dismiss receiver of a bank on grounds of failure to perform his functions in a manner satisfactory to the National Bank.

3/ Expiration of the period of receivership or dismissal of receiver of a bank shall immediately be published by the National Bank in newspapers of wide circulation.

37. Effects of Receivership

Upon the publication of the appointment of a receiver by the National Bank pursuant to Article 33(2) of this Proclamation:

1/ no action may be taken on behalf of the bank without the prior approval of the receiver;

2/ the powers of the shareholders, board of directors and the executive management of the bank shall be suspended and vested in the receiver;

3/ all rights and powers of the bank and all rights and powers that any depositor or creditor has over the bank or its assets shall automatically be vested in the receiver;

4/ the receiver shall take over the assets and the records of the bank and operate it with all the powers of its shareholders, directors and officers and conduct all business of the bank;

5/ any period of limitation, either statutory, contractual, or otherwise, on the expiration of which a claim or right of the bank would expire or be extinguished, shall extend by six months from the date of such expiration;

6/ any existing attachment or lien on any assets of the bank shall be annulled and no new attachment or lien shall be effected to any of the assets of the bank so long as such receivership continues; provided, however, that this provision may not apply to:

ሀ/ ባንኩ በሞግዚት አስተዳደር ሥር ከዋለበት ቀን ከስድስት ወራት በፊት፣ ወይም ለባንኩ ባለአክሲዮን፣ ዳይሬክተር ወይም ሠራተኛ ጥቅም ከሆነ ከ፲፪ ወራት በፊት፣ በተሰጠ የፍርድ ቤት የዕግድ ትዕዛዝ ወይም ዋስትና፣

ለ/ በሞግዚቱ ጥያቄ በፍርድ ቤት በተሰጠ የእግድ ትዕዛዝ ወይም በሞግዚቱ በተሰጠ ዋስትና፣ እና

ሐ/ መጠኑ ብሔራዊ ባንክ ለዚሁ ዓላማ ሲባል ባወጣው መመሪያ ከተወሰነው ጣሪያ በላይ እስካልሆነ ድረስ የሞግዚት አስተዳደሩ ከፀናበት ቀን በፊት በፍርድ ቤት ተወስኖ የአፈጻጸም ትዕዛዝ በተሰጠ በት ጉዳይ፣ ላይ ተፈጻሚ አይሆንም።

፯/ የሞግዚት አስተዳደሩ ከጸናበት ቀን አስቀ ድሞ ባሉት ሦስት ወራት ውስጥ፣ ወይም ለባንኩ ባለአክሲዮን፣ ዳይሬክተር፣ ሰራ ተኛ ወይም ሽሪክ ከሆነ በ፲፪ ወራት ውስጥ፣ የተፈጸመ ማናቸውም ክፍያ ወይም የንብረት ማስተላለፍ ከሌሎች የባንኩ አበዳሪዎች ወይም አስቀማጮች የተለየ ጥቅም የሚያሰጥ ከሆነ ሊጸና አይችልም፣ ሆኖም ይህ ድንጋጌ፤

ሀ/ መጠኑ በብሔራዊ ባንክ ለዚሁ ዓላማ ሲባል ባወጣው መመሪያ ከተወሰነው ጣሪያ በማይበልጥ ለእያንዳንዱ አስቀ ማጭ በተከፈለው የተቀማጭ ገንዘብ ክፍያ፣

ለ/ የንብረቱን የገበያ ዋጋ ግምት ውስጥ በማስገባት ተመጣጣኝ ጥቅም ለባንኩ ለማስገኘት በተደረገ የንብረት ማስተላለፍ፣ እና

ሐ/ የቦነስንና ሌሎች ልዩ ክፍያዎችን ሳይ ጨምር፣ ለባንኩ ዳይሬክተሮችና ሠራ ተኞች በተፈጸመ መደበኛ ክፍያና ጥቅማጥቅም፣

ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም።

፴፰. <u>የሞግዚት መሾምን በመቃወም ስለሚቀርብ አቤቱታ</u>

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፫/፪/ መሠረት ሞግዚት ስለመሾሙ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት ፴ ቀናት ውስጥ ከባንኩ አክሲዮኖች ቢያንስ ፳፭ በመቶ የመምረጥ መብት ያላቸው ባለአክሲዮኖች የሞግዚቱን መሾም በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቤቱታ ማቅረብ ይችላሉ።

a) an attachment or lien existing six months, or twelve months in the case of an attachment or lien in favor of any shareholder, director or employee of the bank, prior to the effective date of the receivership;

b) an attachment or lien created by the receiver; and

c) a writ of execution issued pursuant to a judgment issued prior to the effective date of the receivership, if in an amount not exceeding the limit to be set in directive to be issued by the National Bank for this purpose;

7/ any payment or transfer of an asset of the bank that was made within a period of three months or, if the payment or transfer was made to a shareholder, director, an employee or affiliate of the bank, twelve months before the effective date of the receivership shall be void if it has the effect of bestowing a preference of the recipient over other creditors or depositors of the bank; provided, however, that this provision may not apply to:

a) the payment of deposits in an amount per depositor not exceeding the limit to be set in directive to be issued by the National Bank for this purpose;

b) the transfer of an asset of the bank made in any consideration the value of which is equal to the fair market value of the asset; and

c) the payment of ordinary remuneration and benefits, excluding bonuses and special payments, to the directors and employees of the bank.

38. <u>Appeal against Appointment of Receiver</u>

1/ Shareholders of a bank holding in the aggregate at least 25 percent of the voting shares of the bank may appeal to the Federal High Court against the appointment of a receiver within 30 days after the date on which the receivership is announced in newspaper pursuant to Article 33(2) of this Proclamation.

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ መሠረት አቤቱታ ከቀረበ፤

ሀ/ ፍርድ ቤቱ በአቤቱታው ላይ የመጨረሻ ውሳኔ እስኪሰጥ ድረስ የሞግዚት አስተዳደሩ ይቀጥላል፣

ለ/ ፍርድ ቤቱ አቤቱታው በቀረበ በ፲ ቀናት ውስጥ ጉዳዩን ይሰማል፣ ምርመራውም በተጠናቀቀ በ፳ ቀናት ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል።

፫/ በዚህ አንቀጽ መሠረት አቤቱታ ሲቀርብ በፍርድ ቤቱ መታየት የሚችለው ጭብጥ ብሔራዊ ባንክ ሞግዚቱን የሾመው በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፫ ከተደነገጉት መስፈርቶች አንጻር ሲታይ በዘፈቀደና በግዴለሽነት መሆን አለመሆኑ ብቻ ነው።

፬/ ፍርድ ቤቱ ብሔራዊ ባንክ ሞግዚቱን የሾመው፤

ሀ/ በዘፈቀደና በግዴለሽነት ነው ብሎ ከወሰነ የሞግዚቱ ሹመት እንዲቋረጥ ትዕዛዝ ይሰጣል፣ ወይም

ለ/ በዘፈቀደና በግዴለሽነት አይደለም ብሎ ከወሰነ አቤቱታው ውድቅ ሆኖ የሞግዚት አስተዳደሩ በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት ይቀጥላል።

፴፱. የሞግዚት ሥልጣንና ተግባር

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፫ መሠረት የተሾመ ሞግዚት በሞግዚት አስተዳደር ሥር የዋለውን ባንክ የማስተዳደርና የመቆጣጠር ሙሉና ብቸኛ ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል።

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የሞግዚቱ ሥልጣን የሚከተሉትን ይጨምራል፤

ሀ/ ማናቸውንም የባንኩን ሥራ የመቀጠል ወይም የማቋረጥ፣

ለ/ የባንኩን ንብረቶች የመሸጥ፣

ሐ/ ብሔራዊ ባንክ ስለጉዳዩ በሚያወጣው መመሪያ የሚጥላቸው ገደቦች እንደተጠበቁ ሆነው፣ የባንኩን ንብረት በማስያዝም ሆነ ሳያሲዝ ገንዘብ የመበደር፣

2/ Where an appeal is lodged in accordance with sub-article (1) of this Article:

a) the receivership shall continue until the court delivers a final ruling on the appeal;

b) the court shall hold a hearing on the matter within 10 days of the filing of the appeal, and shall decide the appeal within 20 days of the end of the investigation.

3/ The sole issue to be adjudicated by the court shall be whether the National Bank acted in an arbitrary and capricious manner in establishing the receivership, in light of the criteria set forth in Article 33 of this Proclamation.

4/ If the court determines that the National Bank, in establishing the receivership:

a) did act in an arbitrary and capricious manner, the appointment of the receiver shall be terminated; or

b) did not act in an arbitrary or capricious manner the appeal shall be denied and the receivership shall continue in accordance with the provisions of this Proclamation.

39. Powers and Duties of Receiver

1/ A receiver appointed pursuant to Article 33 of this Proclamation shall be vested with the full and exclusive powers and duties of management and control of the bank under receivership.

2/ Without prejudice to sub-article (1) of this Article, the receiver's powers shall include the power to:

a) continue or discontinue any operations of the bank;

b) dispose of the assets of the bank;

c) borrow money on the security of the assets of the bank, or unsecured, subject to any limitations provided for by directive to be issued by the National Bank for such purpose;

መ/ ባንኩ ያለበትን ማናቸውንም የክፍያ ግዴታዎች የማቋረጥ ወይም የመገደብ፣

ሠ/ በባንኩ ዕዳዎች ላይ የሚከፈሉ የወለድ ተመ ኖችን እንደገና የመወሰን፣ ሆኖም ተመኖቹ በጊዜው አግባብ ባለው ገበያ ላይ ካሉት የወለድ ተመኖች ያነሱ ሊሆኑ አይችሉም፣

ረ/ በማናቸውም የባንኩ ተቀማጭ ገንዘብና ሌሎች ዕዳዎች ላይ ወለድ መታሰብ የሚቋረጥበትን ቀን የመወሰን፣

ሰ/ ማንኛውንም አስፈላጊ የሆነ ባለሙያ ወይም አማካሪ የመቅጠር፣

ሸ/ ባንኩ ተዋዋይ ወገን የሆነባቸውን የሥራ ወይም የአገልግሎት ወይም የኪራይ ወይም ሌሎች ውሎችን የማቋረጥ፣

ቀ/ ባንኩንና የሥራ እንቅስቃሴዎቹን በተመ ለከተ ለወትሮው በሚስጥር ሊያዙ ይችሉ የነበሩ መረጃዎችን ይፋ የማድረግ፣ ሆኖም እንዲህ ዓይነቱ መረጃ ይፋ ሊደረግ የሚች ለው በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፵ ወይም ፵፩ የተገለጹትን እርምጃዎች ለመውሰድ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ብቻ ነው፣

በ/ በባንኩ ስም ማናቸውንም ክፍያ መፈጸ ምና የክፍያ ሰነድ ማውጣት፣ ማናቸው ንም ክስ መመስረት ወይም መከላከልና ማናቸውንም ሌላ ሕጋዊ እርምጃ መው ሰድ።

፫/ ብሔራዊ ባንክ ሞግዚት ሲሾም ሞግዚቱ በቅድሚያ ከብሔራዊ ባንክ ፈቃድ ሳያገኝ ሊወስዳቸው የማይችላቸውን እርምጃዎችና ሞግዚቱ እንዲህ ዓይነቱን ፈቃድ ሲጠይቅ ባንኩ መልስ የሚሰጥበትን የጊዜ ገደብ ሊወስን ይችላል።

፵. የሞግዚት አስተዳደርን ለማጠናቀቅ ስለሚወሰዱ አማራጭ እርምጃዎች

፩/ ማንኛውም የባንክ ሞግዚት፤

ሀ/ የባንኩ ሥራ መቀጠል አዋጪ ሆኖ ካገኘው የሞግዚት አስተዳደሩ ጊዜ እስኪያበቃ ድረስ የባንኩ መደበኛ ሥራ እንዲቀጥል በማድረግ ብሔራዊ ባንክ በሚወስነው ሁኔታና ግዴታ መሠረት ባንኩን ለቀድሞ ባለቤቶቹና ወይም ለቀድሞ ባቤቶቹና ለሽሪኮቻቸው አንዲመለስ ማድረግ፣ ወይም

ለ/ የባንኩ ሥራ መቀጠሉ አዋጪ ሆኖ ካላገኘው ባንኩን በመሸጥ፣ ከሌላ ባንክ ጋር በመቀላ ቀል ወይም በማፍረስ የባንኩ ሥራ እንዲ ቋረጥ ማድረግ፣ ይችላል።

d) terminate or limit any payment obligation of the bank;

e) reset the rates of interest payable on the bank's liabilities; provided, however, that such rates may not be less than those prevailing on the relevant market;

f) set a cut-off date on which accruing interest on deposits and other liabilities terminates;

g) employ any necessary professional or adviser;

h) terminate any contracts of employment, contracts for services, or lease agreements or any other contracts to which the bank is a party;

i) disclose information regarding the bank and its operations that would otherwise be confidential; provided, however, that disclosure shall be made only if it is necessary to take any action specified in Articles 40 or 41 of this Proclamation; and

j) make any payment and execute any instrument in the name of the bank, initiate or defend and conduct in its name any action or legal proceeding.

3/ The National Bank may, upon appointing the receiver, specify certain actions for which the receiver shall obtain prior approval from the National Bank, together with the time period in which such approval shall be either granted or denied.

40. Alternative Actions to Wind up Receivership

1/ Any receiver of a bank may:

a) if the bank is viable, continue the operations of the bank until termination of the receivership and return it to the previous owners, or to previous owners and other partners, under terms and conditions to be determined by the National Bank; or

b) if the bank is not viable, terminate the operations of the bank through acquisition, merger or liquidation.

፪/ በሞግዚቱ የተወሰደው አማራጭ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩/ለ/ የተመለከተው ከሆነ፣ ብሔራዊ ባንክ የባንኩን የሥራ ፈቃድ ወዲያውኑ ይሰርዛል፤ ሆኖም በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፵፮ መሠረት የሞግዚት አስተዳደሩ እስከሚጠናቀቅ ድረስ ባንኩ በስሙ በስተመ ጨረሻው ላይ "በመፍረስ ላይ ያለ" የሚል ሐረግ ተጨምሮበት ሕጋዊ ሰውነቱን እንደያዘ ይቆያል።

፵፩. <u>የባንኩ ሥራ መቀጠል አዋጪ ሳይሆን ሲቀር በሞግዚቱ ስለሚወሰዱ እርምጃዎች</u>

፩/ የባንኩ ሥራ መቀጠል አዋጪ ሳይሆን ሲቀር ሞግዚቱ ብሔራዊ ባንክ በሚወስነው ጊዜ ውስጥ፤

ሀ/ አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ ሌሎች ባንኮች የባንኩን ንብረቶችና ግዴታዎች ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል እንዲወስዱ ያደርጋል፣ ወይም

ለ/ በዚህ አዋጅ ከአንቀጽ ፵፪ እስከ ፵፭ በተደነገገው መሠረት የባንኩን ንብረቶች ሽጦ ያከፋፍላል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ በተመለከተው መሠረት ሞግዚቱ ከሁለቱ አማራጮች አንዱን እርምጃ ለመውሰድ በሚወስንበት ጊዜ በእርሱ አስተያየት የባንኩ ሀብት ከፍተኛ ዋጋ ሊያወጣ የሚችልበትንና የባንዘብ አስቀማጮችንና የሌሎች አበዳሪዎችን ጥቅም ለማስከበር የተሻለውን አማራጭ መውሰድ አለበት።

፫/ ሞግዚቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ መሠረት የመረጠውን እርምጃ ከመውሰዱ በፊት ከብሔራዊ ባንክ ፈቃድ ለማግኘት በጽሑፍ ጥያቄ ያቀርባል። ብሔራዊ ባንክም ጥያቄው በቀረበ በ፲ ቀናት ውስጥ የተመረጠውን እርምጃ መፍቀዱን ወይም አለመፍቀዱን ማሳወቅ አለበት።

፬/ ሞግዚቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩/ሀ/ መሠረት የባንኩን ንብረቶችና ዕዳዎች ሲያስተላልፍ፤

ሀ/ በራሱ አስተያየት ማንኛውም የባንኩ ገንዘብ አስቀማጭ ወይም ሌላ አበዳሪ የሚያገኘው የገንዘብ ድርሻ በዚህ አዋጅ ከአንቀጽ ፵፪ እስከ ፵፭ በተደነገገው መሠረት የባንኩ ንብረት ተሸጦ ከሚደርሰው ገንዘብ የማያንስ ሆኖ ከተገኘ የባንኩን ዕዳዎች ዋጋ ሊቀንስ፣ እና

2/ Where the alternative action stated under sub-article 1(b) of this Article is chosen, the National Bank shall immediately revoke the license of the bank; provided, however, that the bank shall, with the words "under liquidation" added to its name, retain its legal personality until the receivership is concluded in accordance with Article 46 of this Proclamation.

41. <u>Receiver's Actions when the Bank is not Viable</u>

1/ When the bank is not viable, the receiver shall, within a period of time specified by the National Bank, either:

a) arrange for the assumption of some or all of the bank's assets and liabilities by one or more other banks; or

b) liquidate the assets of the bank as provided for in Articles 42 to 45 of this Proclamation.

2/ In determining which course of action to take under sub-article (1) of this Article, the receiver shall select the course of action that is, in his opinion, most likely to result in conserving the greatest amount of the bank's assets and in providing the best protection to the interests of depositors and other creditors.

3/ The receiver shall, before taking the selected course of action pursuant to sub-article (1) of this Article, submit a written request for approval by the National Bank for such course of action. In such a case the National Bank shall, within 10 days, communicate its approval or disapproval to the receiver.

4/ In the course of transferring assets and liabilities in accordance with sub-article 1(a) of this Article, the receiver may:

a) allow a reduction in the value of liabilities so long as, in his opinion, no depositor or other creditor would receive less than he would receive in a liquidation under Articles 42 to 45 of this Proclamation; and

ለ/ ማንኛውም ገንዘብ አስቀማጭ በባንኩ ያለውን ተቀማጭ ገንዘብ ከባንኩ ለተበደረውና ላልከፈለው ገንዘብ ማቻቻያ ሊያደርገው፣ ይችላል።

፵፪. ባንክ ሲፈርስ በቅድሚያ ስለሚፈጸሙ ሥርዓቶች

ማንኛውም ባንክ ሲፈርስ ሞግዚቱ በቅድሚያ፤

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፵፩/፩/ መሠረት ወደ ሌላ ባንክ የሚተላለፉትን ወይም በማጣሪያ የሚሸጡትን የባንኩን ሀብቶች የሚያሳይ ዝርዝር አዘጋጅቶ የዝርዝሩን ቅጂ ለሕዝብ ዕይታ ክፍት ያደርጋል፣

፪/ በአደራ የተቀመጡ ሀብቶችን ለባለቤቶቻቸው ለመመለስና የባንኩን የአደራ ሂሣቦች ለመዝጋት አስፈላጊውን እርምጃ ይወስዳል፣

፫/ በባንኩ መዛግብት መሠረት ማንኛውም ሰው ከባንኩ ስለሚፈልገው ዕዳ የሂሳብ መግለጫ አዘጋጅቶ ይሰጣል፣ ከዚሁ ጋር በማያያዝ በሂሣብ መግለጫው ላይ ተቃውሞ ያለው ማንኛውም ሰው ተቃውሞውን ተገቢ በሆነና ተለይቶ በተገለጸ ጊዜ ውስጥ ለሞግዚቱ ማቅረብ እንደሚችል ማሳሰቢያ ይሰጣል።

፵፫. በይገባኛል ጥያቄዎች ላይ ስለሚሰጥ ውሳኔ

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፵፪/፫/ ከተመለከተው የተቃውሞ ማቅረቢያ የመጨረሻ ቀን በኋላ ባሉት ሁለት ወራት ጊዜ ውስጥ ሞግዚቱ፤

ሀ/ በቀረበው የይገባኛል ጥያቄ አግባብነት ላይ ጥርጣሬ ሲኖረው የይገባኛል ጥያቄውን ውድቅ ያደርጋል፣

ለ/ የእያንዳንዱ ገንዘብ አስቀማጭና ሌላ አበዳሪ ሊከፈለው የሚገባውን የገንዘብ ልክና በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፵፭ ድንጋጌ መሠረት የክፍያውን ቅደም ተከተል ይወስናል፣

ሐ/ የተፈቀዱትን የይገባኛል ጥያቄዎች የሚያሳይ ፕሮግራም ያዘጋጃል።

b) set-off of the deposit liabilities to any depositor against outstanding loan payments owed by that depositor.

42. Preliminary Procedures for Liquidation of Bank

In the case of liquidation of any bank, the receiver shall, in advance:

1/ prepare an inventory of assets of the bank that are to be transferred to another bank or liquidated in accordance with Article 41(1) of this Proclamation and make a copy of the inventory available for examination by the public;

2/ take any necessary steps to return all assets held by the bank as a fiduciary to the owners thereof and settle the bank's fiduciary accounts; and

3/ provide to every person a statement of claim shown on the bank's records in favor of that person, together with a notice that any objection to the bank's records in that respect may be filed with the receiver within a specified reasonable period of time.

43. Decision on Claims

1/ Within two months after the last day for filling objections specified in the notice referred to in Article 42(3) of this Proclamation, the receiver shall:

a) reject any claim if he doubts the validity thereof;

b) determine the amount owed to each depositor and other creditor and the priority classification of the claim under the provisions of Article 45 of this Proclamation;

c) prepare a schedule of allowable claims.

፪/ ሞግዚቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩/ሐ/ የተጠቀሰው ፕሮግራም ለዕይታ የሚቀር ብበትን ቀንና ቦታ እንዲሁም በፕሮግራሙ ላይ ተቃውሞ የሚቀርብበትን የጊዜ ገደብ ማንኛውም የባንኩ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት ባለበት አካባቢ በሰፊው በሚሰራጭ አንድ ወይም ከዚያ በላይ ጋዜጦች ላይ በማምንት አንድ ጊዜ ለሦስት ተከታታይ ሣምንታት አሳትሞ ያወጣል።

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፪/ በተጠቀሰው ማስታወቂያ የሚገለጸው ተቃውሞ የማቅ ረቢያ የጊዜ ገደብ የመጨረሻው ማስታወቂያ በጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ከሯ ቀናት ያነሰ መሆን የለበትም።

፬/ የይገባኛል ጥያቄው ሙሉ በሙሉ ያልተመ ለሰለት ማንኛውም ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፪/ የተጠቀሰው መረጃ በቀጥታ እንዲደርሰው ሞግዚቱ የተቻለውን ጥረት ሁሉ ያደርጋል።

፵፬. ስለተፈቀዱ የይገባኛል ጥያቄዎች የመጨረሻ ፕሮግራምና ድልድል

፩/ ማንኛውም የባንኩ ገንዘብ አስቀማጭ ወይም አበዳሪ ወይም ባለአክሲዮን የተፈቀዱ የይገባኛል ጥያቄዎች ፕሮግራም ይዘትን በተመለከተ የሚኖረውን ተቃውሞ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፵፫/፪/ መሠረት ይፋ ከተደረገው ተቃውሞዎችን የማቅረቢያ የመጨረሻ ቀን በፊት በጽሑፍ ማቅረብ ይችላል።

፪/ ሞግዚቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ መሠረት ተቃውሞ በቀረበ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ በተቃውሞው ላይ ውሳኔ መስጠት አለበት።

፫/ ሞግዚቱ ተቀባይነት ያገኙ ተቃውሞዎችን መሠረት በማድረግ የመጨረሻውን ፕሮግራም ያዘጋጃል። የመጨረሻውን ፕሮግራም ቅጅም ለብሔራዊ ባንክ ያቀርባል።

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፫/ መሠረት የመጨረሻው ፕሮግራም ዝግጅት እንደተጠናቀቀ ሞግዚቱ በተቻለ ፍጥነት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፵፭ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት የመጨ ረሻውን ድልድል ማድረግ አለበት።

2/ The receiver shall publish once a week for three consecutive weeks, in one or more newspapers of wide circulation in every locality where the bank has an office, a notice of the date and place where the schedule referred to in sub-article 1(c) of this Article shall be available for inspection, and the time limit by which any objections to it may be filed.

3/ The time limit to be specified in the notice referred to in sub-article (2) of this Article for filling objections may not be less than twenty days from the date of the last publication of the notice.

4/ The receiver shall make all reasonable efforts to notify directly each person whose claim has not been allowed in full, in order to provide to such person the information referred to in sub-article (2) of this Article.

44. Finalization of Schedule of Allowable Claims and Distribution

1/ Any depositor or creditor or shareholder of the bank may file an objection to the content of the schedule of allowable claims before the final date for objections announced pursuant to Article 43(2) of this Proclamation.

2/ Any objection filed in accordance with Sub-Article (1) of this Article shall be decided upon by the receiver within one month of its filing.

3/ The receiver shall finalize the schedule based on the accepted objections. A copy of the finalized schedule shall be submitted to the National Bank.

4/ As soon as the finalization of the schedule as provided for under Sub-Article (3) of this Article, the receiver shall make final distribution in accordance with the provisions of Article 45 of this Proclamation.

፵፭. የይገባኛል ጥያቄዎች አከፋፈል ቅደም ተከተል

፩/ በማናቸውም የባንክ ንብረት የማጣራት ተግባር በዋስትና የተጠበቁ የይገባኛል ጥያቄዎች ካሉ በተገባላቸው ግዴታ መሠረት መከፈል አለባቸው። ሌሎች በባንኩ ጠቅላላ ሀብት ላይ የሚቀርቡ የይገባኛል ጥያቄዎች አከፋፈል በሚከተለው ቅደም ተከተል መሠረት ተፈጻሚ ይሆናል፤

ሀ/ ለሞግዚቱ የሚከፈለው የአገልግሎት ክፍያና ሞግዚቱ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ለማስፈጸም ያወጣቸው አስፈላጊና አግባብ ያላቸው ወጪዎች፣ ሆኖም ብሔራዊ ባንክ ሞግዚት ሆኖ በሚሠራበት ጊዜ የሞግዚትነት ተግባሩን ለመፈጸም ያወጣው ወጪ ብቻ ታስቦ ተመላሽ ይሆንለታል፣

ለ/ ሞግዚቱ ከተሾመ በኋላ ለባንኩ አዲስ ብድር የሰጡ አበዳሪዎች፣

ሐ/ የሞግዚቱ ሹመት ከፀናበት ቀን በፊት ባለው የሦስት ወር ጊዜ ውስጥ ያለተ ከፈለ የባንኩን የሥራ አስፈጻሚዎች ሳይጨምር የሌሎች ሠራተኞች ደመወዝና ሌሎች ጥቅማጥቅሞች፣ ሆኖም የዚህ ዓይነቱ ክፍያ፤

/፩/ ጉርሻን ወይም ከሚጠበቀውና ከመደበኛው በላይ የሆኑ ክፍያዎችን፣ እና

/፪/ ባንኩ በሞግዚት አስተዳደር ሥር ይሆናል በሚል ግምት አላግባብ የተጨመሩ ክፍያዎችን፣

አያጠቃልልም፣

መ/ ተቀማጭ ገንዘቦች፣

ሠ/ ለፌዴራልና ለክልል መንግሥታት መከፈል ያለበት ታክስ፣

ረ/ በባንኩ ላይ የሚቀርቡ ሌሎች የይገባኛል ጥያቄዎች፣

ሰ/ ሞግዚቱ በሚወስነው ተመን መሠረት በዚህ ንዑስ አንቀጽ በተመለከቱት የይገባኛል ጥያቄዎች ላይ የሚከፈል ወለድ።

፪/ ባንኩ ያለው የሀብት መጠን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ ሥር የተዘረዘሩትን የይገባኛል ጥያቄዎች በሙሉ ለመክፈል በቂ ሆኖ ሲገኝ፣ ቀረው ሀብት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፵፪/፫/ መሠረት በጊዜው ማመልከቻ ላልቀረበባቸውና ተቀባይነት ላላቸው የይገባኛል ጥያቄዎች ክፍያ ይውላል።

45. Priorities in Payment of Claims

1/ In any liquidation of the assets of a bank, secured claims, if any, shall be paid in accordance with their terms. Other claims shall have priority against the general assets of the bank in the following order:

a) remuneration of the receiver and necessary and reasonable expenses incurred by him in implementing the provisions of this Proclamation; provided, however, that in a case where the National Bank is the receiver, it shall be reimbursed only the costs it incurred to carry out the business of receivership;

b) creditors who extended new credit to the bank after the appointment of the receiver;

c) outstanding salaries and other benefits of non-managerial staff of the bank for the three-month period preceding the effective date of the receivership; provided, however, that such payments may not include:

(1) bonuses or payments exceeding the expected and normal amount.

(2) payments which have been added in anticipation that the bank would be put under receivership;

d) deposits;

e) taxes owed to the Federal and Regional Governments;

f) other claims against the bank;

g) interest on claims listed under this sub-article, at a rate to be fixed by the receiver.

2/ If the amount available for payment of claims is adequate to pay all claims listed in sub-article (1) of this Article, any remaining valid claims, which were not filed within the prescribed time pursuant to Article 42(3) of this Proclamation, shall be paid.

፫/ ያለው ገንዘብ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ በተመለከተው በማንኛውም የቅደም ተከተል ደረጃ ሥር ያሉ የይገባኛል ጥያቄዎችን ሙሉ በሙሉ ለማስተናገድ በቂ በማይሆንበት ጊዜ በዚያ ደረጃ ውስጥ ላሉት የይገባኛል ጥያቄዎች ተመጣጣኝ በሆነ ስሌት መከፈል አለበት።

፬/ ሁሉም ተቀባይነት ያገኙ የይገባኛል ጥያቄ ዎች ከተከፈሉ በኋላ ተራፊው የባንኩ ሀብት በባንኩ ውስጥ ባላቸው የባለቤትነት ድርሻ መሠረት ለባለአክሲዮኖች ይከፋፈላል።

፵፮. ስለሞግዚት አስተዳደር መጠናቀቅ

፩/ በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት የባንኩ ንብረቶች በሙሉ ተሸጠው ከተከፋፈሉ በኋላ ሞግዚቱ በአስተዳደሩ ወቅት ስለተከናወኑት ሥራዎች ሪፖርት አዘጋጅቶ ለብሔራዊ ባንክ አቅርቦ ማስጸደቅ አለበት። ብሔራዊ ባንክም የጸደቀውን ሪፖርት ወዲያውኑ ለሕዝብ ይፋ ያደርጋል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ የተመ ለከተው ሪፖርት ለሕዝብ ይፋ እንደተደረገ የሞግዚት አስተዳደሩ እንደተጠናቀቀ ይቆጠ ራል፤ በመፍረስ ላይ የሚገኘው ባንክም ከንግድ መዝገብ እንዲሰረዝ ሞግዚቱ ማመልከቻ ያቀርባል።

፫/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፵፯ መሠረት ክስ ካልተመሰረተ በስተቀር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ የተመለከተው ሪፖርት ለሕዝብ ይፋ በተደረገ በ፴ ቀናት ውስጥ ሞግዚቱና ብሔራዊ ባንክ ከሞግዚት አስተዳደሩ ጋር ከተያያዙ ማናቸውም ግዴታዎች ነፃ ይሆናሉ።

፬/ ጥያቄ ቀርቦባቸውና ተፈቅደው ያልተከፈሉ የይገባኛል ጥያቄዎችን የሚመለከት ገንዘብ ካለ በብሔራዊ ባንክ ዘንድ ይቀመጣል። ሆኖም ብሔራዊ ባንክ የሞግዚት አስተዳደሩ ካበቃበት ቀን ጀምሮ አምስት ዓመት ካለፈ በኋላ ከተቀመጠው ገንዘብ ጋር ከተያያዘ ማናቸውም የይገባኛል ጥያቄ ነፃ ይሆናል።

፵፯. በሞግዚት እርምጃዎች ላይ ስለሚቀርብ አቤቱታ

፩/ ማንኛውም የባንክ ሞግዚት በወሰደው እርምጃ ላይ እርምጃው በተወሰደ በ፴ ቀናት ውስጥ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቤቱታ ሊቀርብ ይችላል።

3/ If the amount available for payment for any class of claims listed in sub-article (1) of this Article is insufficient to provide payment in full, the amount available shall be distributed on a pro rata basis among the claims within that class.

4/ any assets remaining after all claims have been paid shall be distributed among the shareholders in proportion to their ownership in the bank.

46. Conclusion of Receivership

1/ Once all assets of the bank have been disposed of in accordance with the provisions of this Proclamation, the receiver shall prepare an account of the transactions and liquidations carried out under the receivership, and submit it to the National Bank for approval. The National Bank shall, upon its approval, make the account available for public review.

2/ Where the account referred to in sub-article (1) of this Article is made available for public review, the receivership shall be considered concluded; and the receiver shall apply for the registration of the bank under liquidation to be cancelled.

3/ Unless an action has been filed in accordance with Article 47 of this Proclamation, the receiver and the National Bank shall be relieved of any liability in connection with the receivership after 30 days from the date on which the account referred to in sub-article (1) of this Article has been made available for public review.

4/ Any funds, in respect of which claims were made and allowed but not collected, shall be deposited with the National Bank; provided, however, that the National Bank shall be relieved of any responsibility to the claimants after five years from the end of the receivership.

47. Appeal against Actions of Receiver

1/ An appeal against the action of any receiver may be brought before the Federal High Court within 30 days from the date on which such action has been taken.

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ መሠረት አቤቱታ ማቅረብ የሚችሉት የሚከተሉት ሰዎች ብቻ ናቸው፤

ሀ/ ከጠቅላላው ተቀማጭ ገንዘብ ቢያንስ ፳፭ በመቶ ድርሻ ያላቸው ሰዎች፣

ለ/ ገንዘብ አስቀማጮችን ሳይጨምር፣ ከጠቅላላው የይገባኛል ጥያቄ ካላቸው ሰዎች ቢያንስ ፶ በመቶ ያህል ድርሻ ያላቸው አበዳሪዎች፣ ወይም

ሐ/ ከጠቅላላው የባንኩ የተፈረመ ካፒታል ቢያንስ ፳፭ በመቶ ድርሻ የያዙ የባንኩ ባለአክሲዮኖች።

፫/ ፍርድ ቤቱ የቀረበለትን አቤቱታ ሲመረምር ሊያይ የሚችለው ጭብጥ ሞግዚቱ በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት ተግባሩን ሲፈጽም በፍጹም ግዴለሽነትና በዘፈቀደ የሠራ መሆን አለመሆኑን ብቻ ይሆናል።

፬/ ሞግዚቱ ተግባሩን ያከናወነው በፍጹም ግዴለሽነትና በዘፈቀደ ነው ብሎ ፍርድ ቤቱ ሲወስን ሞግዚቱ ካጣ እንዲከፍል ሊያዘው ይችላል፣ ሆኖም ለአቤቱታው ምክንያት የሆነው የሞግዚቱ ድርጊት የሚለወጥ አይሆንም።

፭/ ሞግዚቱ ተግባሩን ያከናወነው በፍጹም ግዴለሽነትና በዘፈቀደ አይደለም ብሎ ፍርድ ቤቱ ከወሰነ ሞግዚቱ ክሱን ለመከላከል ያወጣቸውን ወጪዎች አቤቱታ አቅራቢዎቹ እንዲከፍሉ ያዛል።

፵፰. <u>ስለሌሎች ሕጎች ተፈጻሚነት</u>

የንግድ ሕግና አግባብ ያላቸው ሌሎች ሕጎች ድንጋጌዎች የዚህን ክፍል ድንጋጌዎች እስካልተቃረኑ ድረስ በሞግዚት አስተዳደርና የባንክ መፍረስ ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ።

<u>ክፍል ዘጠኝ</u>
<u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

፵፱. <u>ዕዳ መክፈል በማይቻልበት ወሰን ላይ ስለደረሰ ባንክ</u>

ማናቸውም ዕዳ መክፈል በማይቻልበት ወሰን ላይ የደረሰ ባንክ ተቀማጭ ገንዘብ መሰብሰብ አይችልም።

2/ An appeal under sub-article (1) of this Article may only be brought by:

a) persons representing at least 25 percent of the aggregate amounts of deposits;

b) creditors comprising at least 50 percent in value of the aggregate of the claims of creditors other than depositors;

c) shareholders representing at least 25 percent in value of the aggregate of the subscribed share capital of the bank.

3/ The sole issue to be adjudicated by the court in any such appeal shall be whether the receiver acted in an arbitrary and capricious manner in discharging his functions according to the provisions of this Proclamation.

4/ The court may require the receiver to pay compensation if it determines that he has acted in an arbitrary and capricious manner; provided, however, that the action being challenged may not be reversed.

5/ If the court determines that the receiver has not acted in an arbitrary and capricious manner, it shall order the persons who have brought the action to pay the costs incurred by the receiver in defending the action.

48. <u>Applicability of other Laws</u>

The provisions of the Commercial Code and other relevant laws shall be applicable with respect to receivership and liquidation of banks in so far as they are not inconsistent with the provisions of this Part.

<u>PART NINE</u>
<u>MISCELLANEOUS PROVISIONS</u>

49. <u>Insolvent Bank</u>

Any bank may not accept deposits while it is insolvent.

፶. የባንክ ባልሆኑ ሥራዎች ስለመሠማራት

ባንኮች የባንክ ባልሆኑ ሥራዎች ላይ ሊሠማሩ የሚችሉበት ሁኔታ በብሔራዊ ባንክ በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል።

፶፩. ስለቁጥጥር አገልግሎት ክፍያ

ብሔራዊ ባንክ ቁጥጥር የሚያካሂድባቸው ባንኮች ቁጥጥሩን ለማካሄድ የወጣውን ወጪ እንዲሸፍኑ ለዚህ ጉዳይ ሲባል በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ሊያዝ ይችላል።

፶፪. የይገባኛል ጥያቄ ስላልቀረበባቸው ተከፋይ ሂሳቦች

፩/ ለ፲፭ ተከታታይ ዓመታት የይገባኛል ጥያቄ ያልቀረበበትን፣ በዋና ገንዘቡ ላይ የመጨመር ወይም የመቀነስ እንቅስቃሴ ያልታየበትን፣ የባንክ ደብተር ወይም ሌላ የጽሑፍ መረጃ ያልቀረበበትን ወይም የደብዳቤ ልውውጥ ያልተደረገበትን ተከፋይ ሂሣብ የያዘ ማንኛውም ባንክ በዚሁ ሂሣብ ውስጥ ያለውን ገንዘብ ለብሔራዊ ባንክ ማስተላለፍ አለበት።

፪/ ብሔራዊ ባንክ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ መሠረት ሊተላለፍለት የሚገባውን ዝቅተኛ የገንዘብ መጠንና ባንኮች የዚህ ዓይነቱን ገንዘብ ሲያስተላልፉ ሊከተሉ የሚገባቸውን ሥርዓት በሚያወጣው መመሪያ ይወስናል።

፫/ ማናቸውም ባንክ የይገባኛል ጥያቄ ያልቀረበበትን ተከፋይ ሂሳብ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ መሠረት ለብሔራዊ ባንክ ካስተላለፈበት ቀን ጀምሮ በዕዳው ከመጠየቅ ሙሉ በሙሉ ነፃ ይሆናል።

፬/ ማንኛውም ሕጋዊ ባለመብት ጥያቄ ከአቀረበ ብሔራዊ ባንክ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ መሠረት የተላለፈውን ሙሉውን ገንዘብ ለባለመብቱ መክፈል አለበት፣ ሆኖም በእንደዚህ ዓይነት የይገባኛል ጥያቄዎች ላይ ብሔራዊ ባንክ ወለድ አይከፍልም።

፭/ ብሔራዊ ባንክ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ መሠረት የተላለፉትንና በሕጋዊ ባለመብቶቹ ጥያቄ ያልቀረበባቸውን ሂሣቦች አጠቃቀም በመመሪያ ይወስናል።

50. Engagement in Non-Banking Undertakings

The conditions under which banks may engage in any non-banking undertakings shall be determined by directive to be issued by the National Bank.

51. Inspection Fee

The National Bank may, in accordance with its directive to be issued for this purpose, require banks under its inspection to cover the costs of the inspection.

52. Unclaimed Liabilities

1/ A bank holding any account of liabilities which have not been claimed, the principal balance of which has not increased or decreased, for which pass-book or other records have not been presented or any correspondence has not been made, for 15 consecutive years shall transfer the fund in such account to the National Bank.

2/ The National Bank shall determine by directive, the minimum amount of fund to be transferred to it in accordance with sub-article (1) of this Article and the procedures to be followed by banks in transferring such funds.

3/ Any bank shall, upon the date of transferring unclaimed liabilities to the National Bank in accordance with sub-article (1) of this Article, be fully relieved of such liabilities.

4/ If claimed by any rightful person, the National Bank shall pay to such person full amount of the claim transferred to it under sub-article (1) of this Article; provided, however, that it shall pay no interest on such claims.

5/ The National Bank shall determine by directive the use of funds transferred to it under sub-article (1) of this Article and not claimed by the rightful persons.

፶፫. የደንበኞችን ማንነት ስለማወቅ

ባንኮች የደንበኞቻቸውን ማንነት በትጋት ተከታትለው የሚያውቁባቸውንና አጠራጣሪ የሂሣብ እንቅስቃሴዎችን ሪፖርት የሚያደርጉባቸውን መስፈርቶች ብሔራዊ ባንክ በመመሪያ ሊወስን ይችላል።

53. Know-Your-Customer Standards

The National Bank may issue directive prescribing standards on banks' due diligence in knowing their customers and reporting of suspicious transactions.

፶፬. የባንኮችና የመድን ኩባንያዎች ግንኙነት

፩/ ብድር መስጠትን፣ ተቀማጭ ገንዘብ መቀበልንና የባንክና የመድን አገልግሎቶችን ጨምሮ በባንኮችና በመድን ኩባንያዎች መካከል የሚደረጉ የሥራ ግንኙነቶች በማናቸውም ረገድ ከሌላ ማንኛውም ሰው ጋር ከሚደረጉት የሥራ ግንኙነቶች ጋር ተመሳሳይ በሆኑ ሁኔታዎች መደረግ አለባቸው።

፪/ ብሔራዊ ባንክ በባንኮችና በመድን ኩባንያዎች መካከል የሚኖረውን የሥራ ግንኙነት የሚመለከቱ መመሪያዎችን በየጊዜው ሊያወጣ ይችላል።

54. Relation between Banks and Insurance Companies

1/ Transactions, including the provision of loans and advances, the acceptance of deposits and the provision of banking and insurance services, between banks and insurance companies shall be undertaken on the same terms and conditions as provided to any other person.

2/ The National Bank may issue, from time to time, directives that govern relationships between banks and insurance companies.

፶፭. መረጃዎችን እንዲታተሙ ስለማድረግ

ብሔራዊ ባንክ በዚህ አዋጅ መሠረት የቀረበን ወይም የተሰበሰበን ማናቸውንም መረጃ ወይም ስታትስቲካዊ አሐዞች በከፊልም ሆነ በሙሉ አግባብ ነው ብሎ በአመነበት አቀራረብና ጊዜ አሳትሞ ሊያወጣ ይችላል፣ ሆኖም የጉዳዩ ይፋ መሆን የባንክ ሥርዓቱን ጤናማነት ለማጠናከር ሲባል የሚያስፈልግ ካልሆነ በስተቀር፣ የማናቸውንም ባንክ ወይም ደንበኛ ዝርዝር መረጃ ወይም ስታትስቲካዊ አሐዞች ይፋ ሊያደርግ አይችልም።

55. Publication of Information

The National Bank may publish, in whole or in part, in such form and at such time as it may consider fit, any information or data furnished or collected under this Proclamation; provided, however, that no information or data may be published that might disclose the particular affairs of a bank or of a customer of a bank, unless such publication is in the interest of strengthening the financial soundness of the banking system.

፶፮. የብሔራዊ ባንክ ኃላፊዎችና ተጠሪዎች ከግል ተጠያቂነት ስለመጠበቃቸው

ይህን አዋጅ ለማስፈጸም ሲባል የብሔራዊ ባንክ ኃላፊዎችና ተጠሪዎች በቅን ልቦና ለሚፈጽሙት ማናቸውም ድርጊት በግል በፅዳ ሊጠየቁ፣ ሊከሰሱ ወይም ማናቸውም ሌላ ጥያቄ ሊቀርብባቸው አይችልም።

56. Protection of Officers and Agents of the National Bank from Personal Liability

Any officer or agent of the National Bank may not be subject to any personal liability, action or any other claim for their bona fide acts done for the purpose of carrying out this Proclamation into effect.

፶፯. የብድር መረጃ ልውውጥ ሥርዓት

ብሔራዊ ባንክ በባንኮች መካከል የሚደረግ የብድር መረጃ ልውውጥ ሥርዓት ስለሚደራጅበት ሁኔታ፣ ስለአሠራሩና የወጪ መጋራት መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

57. Credit-Information-Sharing System

The National Bank may issue directives for the establishment, operation and cost apportionment of credit-information-sharing system among banks.

፶፰. ቅጣት

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፫/፩/ የተደነገገውን የተላለፈ ማንኛውም ሰው የጥፋት ድርጊቱ ለቀጠለበት ለእያንዳንዱ ቀን በብር ፳ሺ መቀጫ እና ከ፲ እስከ ፲፭ ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት ይቀጣል።

፪/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፫/፬/ የተዘረዘሩትን ሰነዶች እንዲያቀርብ በብሔራዊ ባንክ ተጠይቆ ያላቀረበ ወይም እምቢተኛ የሆነ ማንኛውም ሰው ከብር ፶ሺ እስከ ብር ፩ሺ በሚደርስ መቀጫ እና ከ፭ እስከ ፯ ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት ይቀጣል።

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ ወይም /፪/ የተመለከተው ጥፋት የተፈጸመው በሕግ የሰውነት መብት በተሰጠው ድርጅት ከሆነ የእሥራት ቅጣቱ ተፈጻሚ የሚሆነው ድርጅቱን በኃላፊነት በሚመራው ሰው ላይ ይሆናል።

፬/ የዚህን አዋጅ አንቀጽ ፲፭ ንዑስ አንቀጽ /፩/ ወይም /፪/ ወይም አንቀጽ ፲፮ ድንጋጌዎችን የተላለፈ ማንኛውም ሰው ከብር ፶ሺ እስከ ብር ፩ሺ በሚደርስ መቀጫ እና ከ፲ እስከ ፲፭ ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት ይቀጣል።

፭/ የዚህን አዋጅ አንቀጽ ፳፰/፭/ ድንጋጌዎች የተላለፈ ማናቸውም የባንክ ዳይሬክተር ከብር ፶ሺ እስከ ብር ፩ሺ በሚደርስ መቀጫ እና ከ፭ እስከ ፯ ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት ይቀጣል።

፮/ ማንኛውም የባንክ ዳይሬክተር ወይም ሠራተኛ፣

ሀ/ ማንኛውም ኦዲተር በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት የተጣሉበትን ግዴታዎች መፈጸም እንዳይችል ወይም በብሔራዊ ባንክ ሥልጣን የተሰጠው ተቆጣጣሪ በባንኩ ላይ ተገቢውን ቁጥጥር እንዳያካሂድ እንቅፋት ከሆነ፣ ወይም

ለ/ ለማታለል በማሰብ የሐሰት ወይም አሳሳች መግለጫ የሰጠ ወይም በባንኩ መዝገብ፣ ሂሣብ፣ ሪፖርት ወይም መግለጫ ውስጥ የመዘገበ እንደሆነ ወይም መመዝገብ የነበረበትን መግለጫ ወይም መረጃ ሳይመዘግብ የቀረ እንደሆነ፣

58 Penalties

1/ Any person who contravenes the provisions of Article 3(1) of this Proclamation shall be punished with a fine of Birr20,000 in respect of each day on which the contravention continues and with a rigorous imprisonment from 10 to 15 years.

2/ Any person who, having been called upon by the National Bank under Article 3(4) of this Proclamation, fails or refuses to submit the documents described therein shall be punished with a fine from Birr50,000 to Birr100,000 and with a rigorous imprisonment from 7 to 10 years.

3/ Where the offence under sub-article (1) or (2) of this Article is committed by a legal entity, the penalty of imprisonment shall be imposed on the person in charge of the management of the entity.

4/ Any person who contravenes the provisions of sub-article (1) or (2) of Article 15 or Article 16 of this Proclamation shall be punished with a fine from Birr50,000 to Birr100,000 and with a rigorous imprisonment from 10 to 15 years.

5/ Any director of a bank who contravenes the provisions of Article 28(5) of this Proclamation shall be punished with a fine from Birr50,000 to Birr100,000 and with a rigorous imprisonment from 7 to 10 years.

6/ Any director or employee of a bank who:

a) obstructs the proper performance by an auditor of his duties in accordance with the provisions of this Proclamation or inspection of a bank by an inspector duly authorized by the National Bank; or

b) with intent to deceive, makes any false or misleading statement or entry or omits any statement or entry that should be made in any book, account, report or statement of a bank;

ሐ/ ባንኩ ዕዳ መክፈል በማይቻልበት ወሰን ላይ መሆኑን እያወቀ ወይም ማወቅ ሲገባው ተቀማጭ ገንዘብ የተቀበለ ወይም ሌላ ሰው እንዲቀበል ያዘዘ ወይም የፈቀደ እንደሆነ፣

ከብር ፶ሺ እስከ ብር ፩ሺ በሚደርስ መቀጫ እና ከ፲ እስከ ፲፭ ዓመት በሚደርስ ፅኑ እሥራት ይቀጣል።

c) knows or ought to know the insolvency of the bank and receives or authorizes or permits the acceptance of a deposit

shall be punished with a fine from Birr50,000 to Birr100,000 and with a rigorous imprisonment from 10 to 15 years.

፯/ ማንኛውም ሰው የዚህን አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎች ወይም ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የወጡ ደንቦችን ወይም መመሪያዎችን የተላለፈ ወይም አፈጻጸማቸውን ያሰናከለ እንደሆነ እስከ ብር ፲ሺ በሚደርስ መቀጫና እስከ ሦስት ዓመት በሚደርስ እስራት ይቀጣል።

7/ Any person who contravenes or obstructs the provisions of this Proclamation or regulations or directives issued to implement this Proclamation shall be punished with a fine up to Birr10,000 and with an imprisonment up to three years.

፶፱. ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

59. Power to Issue Regulation and Directive

፩/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል።

1/ The Council of Ministers may issue regulations necessary for the implementation of this Proclamation.

፪/ ብሔራዊ ባንክ ይህን አዋጅና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ መሠረት የወጡ ደንቦችን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ለማውጣት ይችላል።

2/ The National Bank may issue directives necessary for the implementation of this Proclamation and regulations issued pursuant to sub-article (1) of this Article.

፷. የተሻሩና ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች

60. Repealed and Inapplicable Laws

፩/ የባንክ ሥራ ስለመፍቀድና ስለመቆጣጠር የወጣው አዋጅ ቁጥር ፹፬/፲፱፻፹፮ በዚህ አዋጅ ተሽሯል።

1/ The Licensing and Supervision of Banking Business Proclamation No. 84/1994 is hereby repealed.

፪/ ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ሕግ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የአሠራር ልምድ በዚህ አዋጅ በተደነገጉ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም።

2/ No law, regulation, directive or practice may, in so far as it is inconsistent with the provisions of this Proclamation, be applicable with respect to maters provided for by this Proclamation.

፫/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፪/ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በንግድ ሕግ፣ በመንግሥት የልማት ድርጅት አዋጅ ወይም በሌሎች ሕጎች መሠረት ሊፈጸሙ ከሚገባቸው ግዴታዎች ይህ አዋጅ ባንኮችን ነፃ አያደርጋቸውም።

3/ Without prejudice to the provisions of sub-article (2) of this Article, nothing in this Proclamation shall be construed so as to relieve a bank from compliance with the provisions of the Commercial Code, the Public Enterprises Proclamation or other relevant laws.

፷፩. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ነሐሴ ፲፱ ቀን ፪ሺ ዓ.ም

ግርማ ወልደጊዮርጊስ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

61. <u>Effective Date</u>

This Proclamation shall enter into force up on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa, this 25th day of August, 2008

GIRMA WOLDEGIORGIS

PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA